በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

## ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክና ትርጉም

በዓለም የተለያየ ሐሳብ መጠንና ዕድሜ ያላቸው ዓለማውያት /ስለ ዓለማዊ ሁኔታ የሚናገሩ እና /አምላካውያት /ቅዱሳት/ መጻሕፍት ይገኛሉ:: በዚህ ምዕራፍ አምላካውያት መጻሕፍት በይበልጥ መጽሐፍ ቅዱስን የስሙን ትርጉም፣ ለምን ቅዱስ እንደተባለ፣ በምን ቋንቋ፣ በማን፣ መቼና የት እንደተጻፈ፣ በምዕራፍና በቁጥር የአከፋፈሉን ሁኔታ እንዲሁም ከቋንቋ ወደ ቋንቋ ምሳሌያዊና ምሥጢራዊ ትርጉም ሲባል እንዴት እንደሆነ እንመለከታለን::

<u>ስያሜው</u>፡- መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ቃል የሁለት ቃላት ጥምረት ነው:: «መጽሐፍ» የሚለው ቃል ተጠቃሎ በአንድ ጥራዝ ሥር የተሰበሰበ ጽሑፍን ሲገልጥ፤ «ቅዱስ» የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ክድስ፣ በሱርስት ካዲሀ፣ በግዕዝና በዓረብኛ ቅዱስ ካለው ቃል የተገኘ ነው:: ትርጉሙም የተለየ፣ የተከበረ ማለት ነው::

ቅዱስ /የተለየ/ የተባለበት ምክንያት፡-

1. አስገኝው እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ፣ /ዘሌ. 19÷2/
2. ቅዱሳን ሰዎች የጻፉት በመሆኑ፣ /2ጴጥ. 1÷20-21/
3. የቅዱሳን ክቡር ታሪክና ስም ስለሚገኝበት፣
4. የዕድሜው ርዝማኔና ዘመን የማይሽረው መሆኑ፣ /ኢሳ. 40÷8/
5. ስላለፈውና ስለሚመጣው ነገር በእርግጠኝነት በመናገሩ፣
6. አንባብያኑን የሚሰሙትንና ተከታዮቹን ወደ ቅድስና የሚመራ በመሆኑ ነው:: /ራዕይ 22÷7/

### መጽሐፍ ቅዱስ

- የመንፈስ ምግብ ነው:: /ማቴ. 4÷4፣ ኤር. 15÷16/
- የመንገዳችን መብራት ነው:: /መዝ. 118÷105/
- ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ ነው:: /ዕብ. 4÷12/
- ያነጻል:: /ዮሐ. 15÷3/
- ያስመልጣል:: /መዝ. 1÷3/

### በምን ቋንቋ፣ መቼ ተጻፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ዘመን በአንድ ቦታ በአንድ ሰው ተጽፎ ያለቀ አይደለም:: የሄኖክ መጽሐፍ ከተጻፈበት ከክርስቶስ ልደት 4014 ዓመት በፊት ጀምሮ የሐንስ ራዕይ እስከ ተጻፈበት ድረስ ከ4100 ዓመት በላይ አልፏል:: እንደ ጊዜው መለያየትም ጸሐፊዎቹ አጠራራቸው፣ የተጻፈበትም ቦታዎች የተለያዩ ናቸው::

ምንም እንኳን በዚህ መልኩ ቢለያይም በአንድ መንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ስለጸፉት የሐሳብ መጋጨት የለበትም፡፡ /2ኛጴጥ. 1፥21/

ስምሳሌ፡- ከጸሐፊዎቹ ለመጥቀስ ያህል፡-
- ሰሎሞን ንጉሥ ነበር፡፡ ምሳሌ 1፥1
- ሕዝቅኤል ካህን ነበር፡፡ ሕዝ. 1፥1-3
- አሞጽ እረኛ ነበር፡፡ አሞጽ 1፥1
- ማቴዎስ ቀራጭ ነበር፡፡ ማቴ. 9፥9
- ሉቃስ ሐኪም ነበር፡፡ ቆላ. 4፥14
- ዳዊት እረኛ ነበር፡፡ 1ኛ ሳሙ. 17፥15፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን የልቡን የዋህነትና ቅንነትን ተመልክቶ እንጂ በዕውቀት፣ በውበትና በሀብት አለመሆኑን እንረዳለን፡፡ እንዲሁም የተጻፉት በተለያየ ቦታ ነው፡፡ ስምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| የኦሪት መጻሕፍት | በሲና ምድረ በዳ |
| መጽሐፈ ኢዮብ | |
| መጽሐፈ መሳፍንት | በምድረ ከነዓን /በእሥራኤል/ |
| መጽሐፈ ሕዝቅኤል | |
| መጽሐፈ አስቴር | በፋርስ |
| ትንቢተ ዳንኤል | በባቢሎን |
| መልእክታት | በሮም |
| የዮሐንስ ራዕይ | በፍጥሞ ደሴት |

በዚህ ሁኔታ አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በዕብራይስጥ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ በግሪክ ቋንቋ ተጽፈዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ284 ዓመት በንጉሥ በጥሊሞስ ዘመን መንግሥት በ70 የአይሁድ ሊቃውንት /ሰፕቱ አጊንት/ ከዕብራይስጥ ወደ ልሳነ ግሪክ ሀገር ተተረጎመ፡፡ በሐዲስ ኪዳን ዘመንም እስከ 5ኛው መቶ ክ/ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ይተረጎምባቸው ለመጽሐፍ ቅዱስ ነጠላ ትርጉሜ መሠረታውያን የሆኑ ቋንቋዎች እሉ፡፡ እነርሱም

1. በኢትዮጵያ /ግዕዝ/
2. ሮማይስጥ የጥንቱ ላቲን /ቮልጌት/
3. በግብጽ ቅብጥ /ኮፕት/
4. በሶሪያ /ሱርስት/
5. በአርመን /አርመንኛ/ ናቸው፡፡ በእነዚህ ቋንቋዎች የተተረጎሙት መጻሕፍት በአሁኑ ጊዜ በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸው መሠረታውያን ቋንቋዎች በመሆናቸው በየጊዜው ለሚነሱ ስህተቶች ማረሚያ ስለሚሆኑ ነው፡፡

በጥንት ዘመን ቅዱሳት መጻሕፍት ለንባብ በሚያመች ሁኔታ በክፍል በክፍል ቁጥ ተለይተው ይኖሩ ነበር እንጂ በምዕራፍና በቁጥር ተለይተው የሚነበቡ አልነበረም፡፡ ሉቃስ 4፥16-21፣ 2ቆሮ. 3፥14፡፡

- በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሳው ታላቁ የቤተክርስቲያን አባት አባ ጀሮም ለ40 ዓመታት የዕብራይስጥ የግሪክ ቋንቋዎችን በሚገባ በማጥናት መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ቮልጌት /ሮማይስጥ/ ተርጉሟል።
- ሉተር በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ጀርመንኛ ተርጉሟል። በራሱ አመለካከት ስለተረጎመውና የአባ ጀሮምን ትርጉም ባለመቀበሉ ክካቶሊኮችና በፕሮቴስታንት መካከል አለመግባባት እያየለ ሄዷል።
- በ1525/26 እ.ኤ.አ. ቴንዳሌ የተባለ እንግሊዛዊ የተወሰኑ መጽሐፍትን ወደ እንግሊዝኛ ተረጎመ።
- በዚህ አኳኋን የትርጉሙ ሥራ ቀጥሎ ከ228 ዓ.ም. ጀምሮ በምዕራፍ፣ ከ1551 ጀምሮ ደግሞ ምዕራፎችን በቁጥር መከፋፈል ተጀምሯል።
- ትርጉም ሲባል ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት ከቋንቋ ወደ ቋንቋ፣ ነጠላ ትርጉም፣ ምሳሌያዊና ምሥጢራዊ ትርጉም በመባል አራት ክፍሎች ሊኖሩት ይችላሉ።

1/ <u>ከቋንቋ ወደ ቋንቋ መተርጎም</u>፦ እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም አንድ ከቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የሚተረጉም ሰው ለዚህ ትርጉም ሥራ ከመነሳቱ አስቀድሞ ፈሪሀ እግዚአብሔርን ገንዘብ ማድረግና ብቁ የሆነ የቋንቋ እውቀት ሊኖረው ይገባል። ከእነዚህም ችግሮች የተነሳ ሮሜ. 8፥27 ላይ «መንፈስ ቅዱስ ይራራልናል» የሚለውን «በማይነገር መቃተት ይማልድልናል» በማለት ተርጓሚዎቹ መንፈስ ቅዱስን የተሳደቡ ሲሆን እንዲሁም በሮሜ 8፥34 "ስለ እኛ የሚፈርደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" የሚለውን በሮሜ 8፥34 "ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" በማለት የነበረውን አስወጥተው የሌለ ነገር አስገብተው ጽፈዋል።

2/ <u>ነጠላ ትርጉም</u>፦ መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ ትርጉም የሚወሰዱና ከዚያ የተለየ ምንም ዓይነት ምሥጢራዊ ወይም ምሳሌያዊ ትርጉም የሌላቸው በቀጥታ ሲወሰዱ የሚችሉት በርካታ ኃይለ ቃላት ይገኛሉ። እንደዚህ ላሉት የሚሰጠው ማብራሪያ <u>ነጠላ ትርጉም</u> ይባላል። ለምሳሌ፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብታሪክነት የተመዘገቡ በነጠላ ትርጉም የሚወሰዱ ናቸው። የአብርሃም ከካራን መውጣት፣ የያዕቆብና ልጆቹ ስደት ... ወዘተ

3/ <u>ምሳሌያዊ ትርጉም</u>፦ አንድን ነገር የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የምንጠቀምበት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምሳሌ የተነገሩ በርካታ ክፍሎች ይገኛሉ። የእመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና መኃ.4፥12፣ ሕዝ.44፥1-2፣ የጌታችን በበግ መመሰል ኢሳ.53፥7፣ የጨው ምሳሌ ማቴ.5፥13 የበግና የፍየል ምሳሌነት ማቴ.27፥33 ... ወዘተ

4/ <u>ምሥጢራዊ ትርጉም</u>፦ የተሠወረ ግን በውስጥ ያለ በላይ በላይ የማይታይ ትርጉም ነው። ያለዚህ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክት መጨበጥ አይቻልም።

# ምዕራፍ 2

## የቅዱሳት መጻሕፍት አጠናን ዘዴ

አጥናት ዘዴዎች አንዱ ዘወትር የማንበብ ልምድን ማዳበር ሲሆን፤ ተከታዩ ጥናት ደግሞ ያቃሉን ፍች ብቻ ሳይሆን የትንቢትና ምሳሌዎችን ትርጉም መመርመር ነው።

ለምሳሌ:- ኢትዮጵያዊው የቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ተሳላሚ ጃንደረባ በሠረገላ ላይ ተቀምጦ የትንቢተ ኢሳይያስን መጽሐፍ 53ኛ ምዕራፍ ያነብ ነበር። በዚህም የማንበብ ልምድ የተገኘ ዕውቀት ስለነበረው ዲያቆናዊው ሐዋርያ ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ ጥሪ ድንገት መጥቶ ያነብ የነበረው መሲህ ክርስቶስ ስቤዛ ዓለም በቀራንዮ መስቀል ላይ ስለሚቀበለው መከራ የተጻፈ መሆኑን በማስረጽ ተርጉሞ ባስረዳው ጊዜ ጃንደረባው ምሥጢሩን በቀላሉ ለማስተዋል ከመቻሉ የተነሣ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ተሰጠው ትምህርት በክርስቶስ አምኖ ለመጠመቅ ዝግጁ ሆኖ መገኘቱ ተጽፏል።የሐዋ.ሥራ 8÷26-40።

ቃሉ ሲሰበክ ማዳመጥ ትምህርቱንም ከዕለታዊ ሕይወት ጋር ማዛመድ አንዱ የማጥኛ ዘዴ ሲሆን ሌላው ደግሞ "ሕጌን በልቡናቸው አኖረዋለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። እኔ አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል። ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉና" በማለት እንደተናገረው ሁሉ የቃሉን ትክክለኛ መልዕክት ለማስተዋል የሚያስችልና ወደ እውነት ሁሉ የሚመራ የእግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ የእርሱን ተራዳኢነት ለማግኘት መጸለይም ያስፈልጋል።/ዕብ.8÷10-12፤ ኤር.31÷31/።

በማንበብ ወይም በመስማት መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት በምንፈልግበት ጊዜ፦

- ንጹህ ልብ /1ኛ ጢሞ.1÷5/
- እግዚአብሔርን መፍራት /ፈሪሀ እግዚአብሔር/ ሉቃስ 24÷45፤ 2ኛጴጥ. 1÷20
- መምህራን /የሚመራና የሚያስተምር/ የሐዋ.ሥራ 8÷28-32
- ጸሎትና ተገቢውን ጊዜ መስጠት እንዲሁም ማስታወሻ መያዝ ያስፈልጋል። /ኤፌ.6÷19፤ ቆላ.4÷3-4/

መጽሐፍ ቅዱስን በሁለት ዓይነት መንገዶች መማር ይቻላል። አንደኛው ከመምህራን በአካል መማር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ቀደምት የቤተክርስቲያን አበው ስለ ቤተክርስቲያን የጻፏቸው ድርሰኖቻቸውን በመመርመር ነው። /ሃይማኖተ አበው/

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው፣ የተጻፈበትን ዘመን፣ ባህል፣ የተጻፈበትን ቦታና ሁኔታ እንደተጻፈላቸው ሕዝቦች ታሪክ መሠረት በማድረግ ነው። ስለዚህ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚ /ተርጓሚ/ በከፊልም ሆነ በሙሉ መጽሐፉን የተጻፈበትን ሕዝብ ባህል፣ የመጽሐፉን ታሪክና የተጻፈላቸውን ሕዝቦች ታሪክ መልክዓ ምድራቸውንና የአየሩን ፀባይ ሊያውቅ ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠና ሰው አንድ ጥቅም አገኛለሁ ብሎ መገንዘብ ይገባዋል። በእርግጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅም ዘርዝሮ መዝለቅ ማለት "አባይን በጭልፋ" እንደሚባለው ይሆናል። ጠቅለል ባለ መልኩ ግን አጠቃላይ መልእክት በሚለው ርዕስ ሥር እንደተገለጸው፦

1. የሰው ልጅ በመጽሐፍ ቅዱስ መሪነት ሕይወቱን በሙሉ ተጽፎ ወደ ዘለዓለማዊ ድኅነት የሚደርስበትን መንገድ በመምራት የሚያገኘው ጥቅም ነው። /ዮሐ.20÷31፣ መዝ.1÷18÷105፣ 2ኛጢ.ሞ.3÷13-17/
2. የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ፈቃድ እናውቅበታለን። /ዘፍ.4÷2፣ ማቴ. 22÷37-39/
3. ስለ እግዚአብሔር መገቦትና ሕልውና ማወቅ ነው። /መዝ.134÷6፣ መዝ.102÷19፣ 1ኛጢ.ሞ.6÷15፣ ራዕይ 17÷14፣ መዝ. 146÷8-9/

**ጥያቄ**

1. የሚከተሉትን ጥቅሶች በምህጻረ ቃል ከጻፍክ በኋላ በሌላ መጽሐፍ የሚገኙበትን ቦታ በምህፃረ ቃል ጥቀስ።
   ሀ/ ወደ ዕብራውያን ምዕራፍ 12 ቁጥር 5 እና 6
   ለ/ የይሁዳ መልዕክት ቁጥር 14 እና 15

## ምዕራፍ ሦስት

## የቅዱሳት መጻሕፍት አሰያየም አቀማመርና አንዳንድ ጥያቄዎች

መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት መድብል ነው። በአንድ ወቅት ብቻ ተጠርዞ የተገኘ ወይም የተሰጠ አይደለም። ስለሆነም የእያንዳንዱ መጻሕፍት ስም /አሰያየም/ የተለያየ ነው።

ሀ/ በጸሐፊው ስም የሚጠሩ መጻሕፍት፡-
- መጽሐፈ ኢያሱ
- መጽሐፈ ሄኖክ
- መዝሙረ ዳዊት
- የጴጥሮስ መልዕክት ወ.ዘ.ተ

ለ/ ከይዞታቸው መጽሐፉ የሚይዘው ሀሳብ በመነሳት ስም የተሰጣቸው መጻሕፍት፡-
- መጽሐፈ ኦሪት
- መጽሐፈ ኩፋሌ
- መጽሐፈ አስቴር
- መጽሐፈ ነገሥት
- መጽሐፈ መሣፍንት ወ.ዘ.ተ

ሐ/ በጸሐፊውና በይዞታቸው የሚጠሩ፡-
- መኃልዬ መኃልይ ዘሰሎሞን
- ትንቢተ ኢሳይያስ
- የማቴዎስ ወንጌል
- የዮሐንስ ወንጌል

መ/ በሀገር /በከተማ/ ስም የሚጠሩ፡-
- ወደ ሮሜ ሰዎች መልዕክት /የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት

ሠ/ በተላከላቸው ሰዎች ስም የሚጠሩ፡-
- ቲቶ፣ 1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ፣ ፊልሞና

ቅዱሳትም መጻሕፍትን መሰብሰብ የተጀመረው የመጀመሪያው መጽሐፍ ከተጻፈበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑ ግልጥ ነው። ሆኖም ብዛታቸውንና ዓይነታቸውን ለይቶ ለማወቅ ሲባል በተለይ በሐዲስ ኪዳን ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። ከዚህም ሌላ በ325 ዓ.ም. በኒቅያ በተካሄደው ጉባኤ ላይ

ከዚያም በኋላ በሎዶቅያ ጉባዔና በ393፣ 399 እና በ419 ዓ.ም. በሰሜን አፍሪካ ትገኝ በነበረችው ቅርጣግና /ካርቴጅ/ በተካሄዱት ጉባዔዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ተደርጓል። ከዚህ ጉባዔ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን በአንድ ላይ መጠረዝ እንደተጀመረ ይነገራል። የሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍትን መድብል /ጥራዝ/ በአንድነት "መጽሐፍ ቅዱስ" ተብሎ ይጠራል። ይህም መጽሐፍ የ81 /ሰማንያ ወአሐዱ/ መጽሐፍት መድብል ሲሆን ብዛቱም በ318ቱ ሊቃውንት የተወሰነ ነው። /ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሁለት/

ሰማንያ አንዱም መጻሐፍት በ325 ዓ.ም. በጉባዔ ላይ እንደተወሰነ ተካትተው የተጠረዙ አይደሉም። ምክንያቱም በወቅቱ በዓለማዊ ፍልስፍና እየተበረዙ ያሉት መጻሕፍት ላይ ብቻ ትኩረት በመስጠቱ፣ መጽሐፍቱ የተቀመጡበት ቦታ ቆይቶ በመታወቁ /ዕዝ. ሱቱኤል 11:37/ ፣ እንዲሁም ከመጻሕፍቱ ውስጥ አንዳንዶቹ በይዘታቸው ትላልቅ በመሆናቸው ራሳቸውን ችለው እንዲቀመጡ በመደረጉ ነው።

እነዚህ 81 መጻሕፍት በ66ቱ መጻሕፍት ላይ ማለትም በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ በመጨመር የሚሟሉ ናቸው።

| የብሉይ ኪዳን | ሐዲስ ኪዳን |
|---|---|
| ❖ መጽሐፈ ኩፋሌ | ❖ ሥርዓተ ጽዮን ሲኖዶስ |
| ❖ መጽሐፈ ሔኖክ | ❖ ትዕዛዝ ሲኖዶስ |
| ❖ መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል | ❖ ግፅው ሲኖዶስ |
| ❖ መጽሐፈ ጦቢት | ❖ አብጥሊስ |
| ❖ መጽሐፈ ዮዲት | ❖ 1ኛ መጽሐፈ ኪዳን |
| ❖ መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ | ❖ 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን |
| ❖ መጽሐፈ መቃብያን ዳግማዊና ሣልሣዊ | ❖ ቀሌሜንጦስ |
| ❖ መጽሐፈ ሲራክ | ❖ ዲድስቅልያ |
| ❖ መጽሐፈ ጥበብ | |
| ❖ መጽሐፈ የሲፍ ወልደ ኮርዮን | |

በ1980 ዓ.ም. በታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ለብቻቸው የተቀመጡ መጻሕፍት አሉ። ምንም እንኳን ለብቻ ተዘርዝረው መጠሪያ ስም ተሰጥቷቸው ቢገኙ አቆጣጠራቸው ግን ወደ እናት መጻሕፍቶቻቸው እየገቡ ነው። ይህም ማለት ለየብቻ በየራሳቸው እንደ አንድ መጽሐፍ አይቆጠሩም ማለት ነው።

ሌሎች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ውጭ የሆኑትም አይሁድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን፣ ሳምራውያን 5ቱን የሙሴ ሕግ መጻሕፍትን ሲቀበሉ ካቶሊክ 73፣ የግሪክ ኦርቶዶክስ 76/77/ ፕሮቴስታንት 66፣ የራስል ተከታዮች /ጆሆባውያን/ የ1000 ቃላት ዕርማት ሰጥተው 66 መጽሐፍትን ይቀበላሉ።

አንዳንድ የሃይማኖት ድርጅቶች /መናፍቃን/ ከላይ የጠቀስናቸውን መጻሕፍት በሙሉ ላለመቀበል የሚሰጧቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. አይሁድ አልተረከቧቸውም ሰባው ሊቃውንትም ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ዕርዕ ሲተረጉሙ አልተረጎሟቸውም:: መጻሕፍቱም የተገኙት ከአይሁድ ስለሆነ እነርሱ ያልተቀበሉትን እንዴት እንቀበላለን? የሚል ነው::

- ይህን ጥያቄ ለመመልከት አይሁድ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቀኖና ከወሰኑበት ስንነሳ አይሁድ ጌታችንን ጠልተውትና ተመቅኝተው አሳልፈው ቢሰጡትም በትንሣኤው ነገራቸውን አፈረሰባቸው:: ባረገ በ10ኛው ቀን ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው አይሁድ ከያዟቸው መጻሕፍት የተነገሩ ትንቢቶችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸሙን ያስተማሩበትና አይሁድ ለሚጠይቋቸው መልስ በመስጠት ያሳፈሩበት ጊዜ ነበር:: /የሐዋ.ሥራ 5÷17-12/፣ የሐዋ.ሥራ 7÷1-60/ በዚሁ የተረበሹት አይሁድ የተጠቀሙበትንና ግልጽ ትንቢት ያለባቸውን ለማጥፋት በጉባዔ ወስነው በተለይም በዕብራይስጥ ብቻ የተጻፉትን አቃጥለዋቸዋል:: ለምሳሌ ሕዝቅኤል አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ካለው ሌላ የትንቢት መጽሐፍ የነበረውን በዚሁ ጊዜ ጠፍቷል::

እንዲሁም የግሪኩ ትርጓሜ ያሳቸውን እንደ መጽሐፈ ሄኖክ በሙት ባህር አካባቢ ሲገኝ በዕብራይስጥ ቋንቋ ሆኖ መገኘቱ በአይሁድ ዘንድ ተቀባይነት እንደነበረው ከመረጋገጡም በላይ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከሚገኘው ጋር ተመሳክሮ አንድነት ስለነበረው በተለያዩ ቋንቋዎች እንዲጻፍ ተደርጓል::

ከዚህም በተጨማሪ በግሪኮች ዘንድ መጽሐፈ ሶስና፣ መዝሙር ዘሰለስቱ ደቂቅ እና ተረፈ ዳንኤል /ቤል ወደራጎን/ ልክ እንደኛ አቆጣጠር ከትንቢተ ዳንኤል ጋር ተጨምረው ይቆጠራሉ:: ስለዚህ እነዚህን መጻሕፍት ሰብዓው ሊቃናት አልተረጉሟቸውም ነበር የሚል ሐሳብ ከንቱ ፈጠራ መሆኑን ልብ ይሏል:: በተጻፉበት በእናት ቋንቋቸው /በዕብራይስጥ/ ተጽፈው ሳያገኛቸው ሊተረጉሟቸው አይችሉምና::

2. መጻሕፍቱ ታምኖባቸው ቢሆን ኖሮ የሐዲስ ኪዳን ጸሐፍያን ከእነዚህ መጻሕፍት አንዳንድ ጥቅሶች በጠቀሱ ነበር:: ነገር ግን ምንም የተጠቀሰ የለም::

- በመሠረቱ አንድ መጽሐፍ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ በግድ በሐዲስ ኪዳን መጠቀስ አለበት የሚል የሃይማኖት ዶግማ አልተደነገገም:: እንደዚህም ቢሆን ከመጽሐፈ አስቴር፣ ከመኃልይ መኃልይ፣ ከመጽሐፈ መክብብ፣ ከመጽሐፈ ሩት፣ ከመጽሐፈ መሳፍንትና ከ1ኛ ዜና መዋዕል በሐዲስ ኪዳን የተጠቀሰ ጥቅስ ስለመኖሩ ተቀባይነት የሌላቸው መጻሕፍት ናቸው በተባሉ ነበር:: እንዲያውም ከእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ተመሳሳይ ሐሳብ ያላቸው መጻሕፍት አሉ:: ለምሳሌ የሚከተሉትን ጥቅሶች ማመሳከር በቂ ይሆናል::

| | |
|---|---|
| ጦቢት 4÷9 ........................................ | ማቴ. 6÷19 |
| ጦቢት 7÷4-16 ........................................ | ማቴ. 7÷12 |
| ዮዲት 8÷12 ........................................ | ማቴ. 4÷7 |
| 2ኛመቃ. 14÷7 ........................................ | ማቴ. 22÷23-33 |
| 2ኛመቃ. 17÷1-6 ........................................ | 1ኛ ቆሮ. 15÷35-48 |
| ሲራክ 28÷4 ........................................ | ማር.11÷25፣ ሉቃስ 6÷37 |

ከዚህ በተጨማሪም የሐዲስ ኪዳን ጸሐፊያን በቀጥታ ጠቅሰው የተጠቀሙበት ቦታ እናገኛለን:: ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች ማገናዘብ በቂ ነው::

ሄኖክ 1÷9፤ ይሁዳ 14 እና 14

ተረፈ ኤር. 7÷3፤ ማቴ. 7÷9

ቅዱሳት መጻሕፍት ከላይ የጠቀስናቸው 81 ብቻ አይደሉም:: የሃይማኖት ሥርዓትና ዶግማ በጽሑፍ፣ በቃልና በተግባር ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ ሲተላለፍ ኖሯል:: ይኸውም ቅብብል ትውፊት ይባላል:: ቤተክርስቲያናችን የጽሑፍን በጽሑፍነቱ፣ የቃሉን በቃልነቱ፣ የተግባሩንም በተግባርነቱ ትቀበለዋለች:: የእምነት፣ የታሪክ፣ የባህል ትውፊቶች አሉ::

ትውፊት ቃል በቃል ይተላለፍና ሊቃውንት ይጽፉታል ወይም ሳይጻፍ ቃል በቃል ይተላለፋል:: በሕገ ልቡና የተደረገው ለሕገ ኦሪት ይተላለፋል:: ከሕገ ኦሪትም ወደ ሕገ ወንጌል የተላለፈ ትውፊት አለ:: በነብያትም በኦሪትም ሳይጻፍ በሐዋርያት ጊዜ የተጻፈ እናገኛለን:: ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ጽፎለታል:: 2ኛ ጢሞ. 3÷8 / እንደዚሁም በዘመነ ወንጌል ፈጽሞ በሐዲሳት መጽሐፍ ሳይጻፍ በአበው ሐዋርያትና በሊቃውንት ዘመን የተጻፉ አሉ::

| | | |
|---|---|---|
| ለምሳሌ፣ | ነገረ ማርያም | ቅዳሴ ማርያም |
| | ተአምረ ማርያም | ገድለ ጊዮርጊስ |
| | ውዳሴ ማርያም | ገድለ ተ/ኃይማኖት ወ.ዘ.ተ. |

ያለ ትውፊታዊ መረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን ሙሉ የማይሆንበት ጊዜ እንዳለ ማወቅም ተገቢ ነው:: ከላይ የጠቀስነው የቅዱስ ብሂል አንድ አስረጅ ሊሆን ይችላል::

# ምዕራፍ ሁለት

## መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ እግዚአብሔርን በማምለክ ትኖር የነበረች ቅድስት ሀገር ስለመሆንዋ ብዙ የታሪክ ጸሐፊዎችና ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክሩላታል:: 70 ሊቃውንት የተረጎሙት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አስቀድሞ በቀደማዊ ምኒሊክ ዘመን በ982 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ትውፊታዊ ታሪክ አለ:: ይህን የብሉይ ኪዳን ሕግና ሥርዓት ጠብቃ ከቆየች በኋላ የክርስትና ሃይማኖትን የተቀበለችው ከ34-35 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ነው:: ሐዋ.8÷26 ላይ እንደተጠቀሰው የንግሥት ህንደኬ ባለሟል የነበረው ጃንደረባ ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሄደ እንደመለከታለን:: ከዚያም የእግዚአብሔር መልዓክ ፊልጶስን አዞ በፊልጶስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ አዲሱን ሃይማኖቱን ለሀገሩ ሕዝብ አስተምሯል:: የኢሳይያስን መጽሐፍ ይዞ መገኘቱም ኢትዮጵያ ከክርስትና ጊዜ አስቀድሞ ቅዱሳት መጻሕፍቱን እንደምትጠቀም ያሳያል::

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ፍሬምናጦስ 330 ዓ.ም. በእስክንድርያ ፓትሪያርክ በአትናቴዎስ እጅ ተሹሞ ጃንደረባው በመሠረተው ላይ ክርስትናን በማጠናከሩ በተጨማሪ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከእብራይስጥና ከዕርብ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መልሷል::

በቢዛንታይን መንግሥት ስቃይ የበዛባቸው ዘጠኙ ቅዱሳን መነኮሳት ከሶሪያ ከታናሽዋ እስያ ተሰደው በ480 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የሀገሪቱን የግዕዝ ቋንቋ ተምረው አያሌ መጽሐፍትን ከሱርስት፣ ከዕርዕ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ከመመለሳቸው በተጨማሪ 70 ሊቃውንት የተረጎሙትን መጻሕፍት ይዘው መጥተዋል።

ከዚያም በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አባ ሰላማ /መተርጎም/ ሐዲስ ኪዳንን ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል። አባ አብርሃም /ግብጻዊ አባ ሮሜ ይሏቸዋል/ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ሊቅ ከጎንደር ተነስተው ወደ ግብፅ በመሄድ የተለያዩ ቋንቋዎችን በማጥናት ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማርኛ ተርጉመዋል። ከዚህም ትርጉም በ1816 ዓ.ም. አርባዕቱ ወንጌላት /አራቱ ወንጌሎች/ በ1821 ዓ.ም. ሐዲስ ኪዳን በ1832 ዓ.ም. ደግሞ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞ ወጥቷል። ከዚያ ወዲህ በ1878 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሊቃውንት የዕብራይስጡንና የግሪኩን ቋንቋ ከሚያውቁ የውጭ ሀገር ዜጎች ጋር በመሆን /ለምሳሌ ማርቲን ፍላድ/ እንደገና በማገናዘብ እንዲታተም ተደርጓል።

ስለዚህ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት እና ትርጉም አስተምራለሁ ማለት "ለቀባሪው አረዱት" እንደሚባለው ይሆናል። እንዲህ አድርጋ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሥር ከሥር የተቀበለች በመሆንዋ ለሁሉቱም ኪዳናት ብቸኛ ባለቤት የሆነችው ሀገራችን ለሰማንያ አሀዱ ቅዱሳት መጻሕፍትም ብቸኛ ባለቤት ናት። ሌሎች መጻሕፍት እንደሃይማኖተ አበው፣ ድርሳናትና ፍትሐ ነገሥት መጻሕፍት በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል።

ከላይ በተገለጹት የታሪክ መሠረትነት ቅድስት ሀገራችን በባህል የምትመራ ብቻ እንዳይደለች እንረዳለን። ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ፣ በመጻፍ፣ በመዳሰስ ፈውስ እናገኝበታለን። የልዑል እግዚአብሔር ቃል ኃይል አለውና። እነዚህንም መጻሕፍት በቃል፣ በሥርዓት በምግባር ታስተምረዋለች፤ ሥርዓትዋ አሠራርዋ አልባሳትዋ ሁሉ ትምህርተ ወንጌል ይዘዋልና።

የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍት በሁለት ክፍሎች ይገኛሉ።

1. በሀገር ውስጥ የሚገኙ
   - በግለሰቦች እጅ
   - በጥንታውያን አድባራትና ገዳማት ዕቃ ግምጃ ቤቶች
   - በዘመናዊ ሙዚየም /ቤተ መዘክር፣ ቤተ መጻሕፍት /በቤተክርስቲያናት/ ለምሳሌ:- ዝዋይ፣ ጽዮን ማርያም፣ መናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ እንጦጦ ማርያም
   - በሀገሪቱ ባሉ ዓብያተ መዘክርና ዓቢያተ መጻሕፍት
   - አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት
   - ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር

ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች ውስጥ ዘጠና በመቶ የሚሆኑት መጻሕፍት በግዕዝ ቋንቋ በጥንታዊ የብራና የአጻጻፍና የአጠራረዝ ዘዴ የተጻፉ ናቸው።

2. ከሀገር ውጭ
   - በግለሰቦች እጅ
   - በአብያተ ክርስቲያኑ፣ መዘክሩና፣ መጻሕፍት የሚገኙ

እነዚህ በውጭ ሀገር የሚገኙ መጻሕፍት በሰጦታ፣ በመገለበጥ፣ በዝርፊያ የወጡ ናቸው።
የኢትዮጵያ መጻሕፍት በአሥር ክፍላት ልናያቸው እንችላለን።

1. መጽሐፍ ቅዱስ፣ 46 የብሉይ ኪዳን 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት
2. የትርጓሜ መጻሕፍት፣ ብሉይና ሌሎችም የተተረጎመባቸው መጻሕፍት
3. ነገረ ሃይማኖት መጻሕፍት፣ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው መጻሕፍት እንደሃይማኖተ አበው፣ ሕጽማደ ምሥጢራት፣ ክብረ ቅዱሳን ... ወዘተ
4. የጸሎት መጻሕፍት፣
   ሀ/ ለአገልግሎት - ምሥጢራት ሲፈጸሙ መጽሐፈ ክርስትና መጽሐፈ ተክሊል፣ የተለያዩ ሰሞናት የሚነበቡ ግብረ ሕማማት ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣
   ለ/ ለፀወትር - ውዳሴ ማርያም፣ ውዳሴ አምላክ፣ መልክአ ጊዮርጊስ፣ ሰዓታት
5. የሥርዓት መጻሕፍት፣ ፍትሐ ነገሥት፣ መጽሐፈ ግጻዌ፣ መጻሕፍተ መነኮሳት
6. የታሪክ መጻሕፍት፣ ክብረ ነገሥት፣ ታሪክ ነገሥት፣ የዋልድባ ታሪክ፣ መጽሐፈ ጤፉት
7. የጥበብ መጻሕፍት፣ አክሲማሮስ፣ መጽሐፈ ሥነ ፍጥረት፣ አቡሻክር
8. ገድላት፣ ገድለ ተክለሃይማኖት፣ ገድለ ጊዮርጊስ፣ ገድለ ጻድቃን
9. ድርሳናት፣ ድርሳነ ዑራኤል፣ ድርሳነ ገብርኤል፣ ድርሳነ ሚካኤል ... ወዘተ
10. ተአምራት፣ ተአምረ ማርያምና ተአምረ ኢየሱስ ናቸው።

አንድ መጽሐፍ በቤተክርስቲያናችን ቅዱስ የሚለውን ስያሜ የሚያገኘው:-

1. መጽሐፉ የተጻፈው በመንፈስ ቅዱስ በተቃኙ አበው መሆኑ ሲረጋገጥ
2. መጽሐፉ የተጻፈው ስለ ቅዱሳን ሲሆን
3. መጽሐፉን ቤተክርስቲያን በጽሑፍተ ቀኖናዋ ስትቀበለው ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## የመጽሐፍ ቅዱስ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍና የሁለቱ ኪዳናት ግንኙነትና ኅብረት

ብዙ ዓለማውያን መጻሕፍት ተወዳጅነትና ብዙ አንባብያን ካገኙ በኋላ በተወሰኑ ዓመታት ያልፋሉ ብሎም አብዛኛዎቹ ይረሳሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን መጽሐፉ ከተጀመረበት እስከ አሁን ድረስ ከ5000 ዓመታት በላይ ሲሆነው ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ ብዙ አንባቢዎችንና ተማሪዎችን ያገኘና በብዙ ቋንቋዎች ተባዝቶ የተሠራጨ መጽሐፍ ነው። እንዲህ የሆነበት ምክንያትም:-

1. የዘለዓለም አምላክ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ስለሆነ ቃሉ ግን አያልፍም /ኢሳ. 40÷3/።
2. በእግዚአብሔር አምነው በጻኑ አባቶች ስክብር ይቀመጡና ይጠበቁ ስለነበር /ዘዳ. 31÷23-29 ሉቃስ 4÷10-19/ ይህም ሲባል፣

• በብራና፣ በጡብ ወዘተ እየተጻፉ በማብዛት፣

- ኦረማውያን ከዛድያን ቤተመቅደስንና ቤተክርስቲያንን ሲያወድሙ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲያጠፉ አበው መጽሐፍቱን ይዘው ጉድጓድ ምሰው፣ በየዋሻው በመቅበር ሕይወታቸውን ሰጥተው ለተተኪው ትውልድ ታላቁን ሀብታቸውን በማቀበል፣

3. ሊቃውንት አባቶች አበው በቃል ንባብ ያጠኑትን ከመከራ በኋላም ሆነ በየጊዜው በመጻፍ አቆይተዋል።

አስቀድሞ እንደተገለጸው መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ተከፍሉ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን በመባል ይታወቃል። ከብሉይ ኪዳን ጋር የተያያዙና በመሠረቱ ቁም ነገር ሁሉ የተሳሰረ ስለሆነ አይለዩም። ሁለቱንም ለማስተማር ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሱ ማስረጃዎች በሐዲስ ኪዳን ውስጥ 614 ጊዜ ባላነሱ አንቀጾች ተወራርሰው ይገኛሉ። እግዚአብሔር ሰውን ከወደቀበት አዘቅት ለማዳን በተገለጸው መንገድ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት የተዛመደና በፍሬ ነገሩ የተሳሰረ መንገድ ገልጸልናል። ሙሴ፣ ኢሳይያስ፣ ዳንኤል፣ ሚክያስን ሌሎችም ነቢያት ስለ አንድ መድኅን ወደዚህ ዓለም መምጣት አስቀድመው ትንቢት ተናግረዋል። ይህ የዓለም መድኅን ክርስቶስም የእነሱን ትንቢቶች በመጥቀስ በዓለም ላይ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ በፈጸመው የማዳን መንገድ አስረድቷል። ስለ ብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትም "እናንተ በመጻሕፍትም የዘለዓለም ሕይወት ያላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ። እነርሱም ስለ እኔ የመሰክሩ ናቸው። ሙሴንስ ብታምኑ እኔን ባመናችሁ ነበር እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?" ብሏቸዋል። ዮሐ. 5÷36፣46-47።

ትንቢተ ኢሳይያስ ስለ ሥራው አስቀድሞ የጻፈውን ከሚያምኑት መጽሐፍ ገልጾ ካነበበ በኋላ በናዝሬት ቤተ ምኩራብ ለተሰበሰቡት እንዲህ ሲል አስረዳቸው። "ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ።" ኢሳ.6÷11፣ ሉቃስ 4÷17-24። ለዲያብሎስ ሳቀረበለትም ጥያቄ ተጽፏልና ብሎ አስረድቷል። ማቴ.4÷4፣ ማቴ.4÷7፣ ማቴ.4÷19 ከብሉይ ኪዳንም የጠቀሳቸው ጥቅሶች ዘዳ.8÷3፣ ዘዳ.6÷16፣ ዘዳ.6÷13 ናቸው። ሌሎችም የሚገናዘብያ ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው። ሉቃስ 24÷25-27፣ ዘዳ.18÷15፣ ኢሳ.53፣ ኤር.23÷5-6፣ ሚክ.5÷2፣ ሉቃስ 24÷46-47፣ መዝ.21÷1፣ ኢሳ.53÷3-5፣ ዮሐ.20÷9፣ ኢሳ.2÷2-3፣ ማቴ.24÷14።

ጌታችንም ቅዱሳት መጻሕፍትም እንዳይሻሩ አስቀድሞ አስታውቋል። ማቴ.5÷17-20። "እኔ ሕግንና ነቢያትን ልሽር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።" ስለዚህ ጌታችን ሥጋን ለብሶ ወደዚህ ዓለም በመምጣቱ በራሱ መሥዋዕትነት ከተሻሩት ነገሮች በስተቀር ሌላ የተሻረ ነገር ወይም ሕገ ልቡና አይገኝም።

# ምዕራፍ ስድስት

## የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከተጻፉበት ጊዜ ፤ ከያዙት ሐሳብና ከአጻጻፋቸው ሁኔታ የሕግ፣ የታሪክ፣ የመዝሙርና የትንቢት ክፍል ተብለው በአራት ይከፋፈላሉ።

## የሕግ መጻሕፍት

ኦሪት፡- ቃሉ የሱርስት ሲሆን ብርሃን ማለት ነው። በዕብራይስጥ ቶራ፣ በግሪክ /ፅርዕ/ ኖምስ ይባላል። ትርጉሙም ሕግ ማለት ነው። "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴም ብርሃን ነው። "መዝ.118፥105 እንዲል በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ከሚለው ጋር ተያይዘው የሚጠሩ 5 መጻሕፍት አሉ።

1. ኦሪት ዘፍጥረት
2. ኦሪት ዘጸአት
3. ኦሪት ዘሌዋውያን
4. ኦሪት ዘኁልቁ
5. ኦሪት ዘዳግም

ሲሆኑ እነዚህ መጻሕፍት በሊቀ ነቢያት ሙሴና በሲና ምድረ በዳ ከጌታ ልደት 1400 ዓመት በፊት የተጻፉ ናቸው።

## ኦሪት ዘፍጥረት

የሥነ ፍጥረትን አፈጣጠር በመግለጽ ስለሚጀምር "ዘፍጥረት" ተብሏል። ኦሪት "ዘልደት" በመባልም ይጠራል። 50 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው። ይዘቱም፡-

1. ከምዕ. 1-5 የሥነ ፍጥረት አፈጣጠር፣ የሰው ልጅ ውድቀትና የመጀመሪያዎቹ አባቶች ዕድሜ፤
2. ከምዕ. 6-11 የሰው ልጅ በኃጢአት መከፋትና ቅጣቱ፣ ስለ ባቢሎን ግንብ፤
3. ከምዕ. 12-26 የአብርሃም የእምነት ጉዞ፣ የሰዶምና ገሞራ ጥፋትና የይስሐቅን ታሪክ፤
4. ከምዕ. 27-50 የያዕቆብና የዮሴፍ ታሪክ፣ የእሥራኤልም ወደ ግብፅ መውረድ።

## ኦሪት ዘጸአት

ዘጸአት የግዕዝ ቋንቋ ቃል ሲሆን መውጣት፣ መመለስ ማለት ነው። የእሥራኤልን ከ430 ዓመት በኋላ ከግብፅ መውጣት ስለሚያወሳ ዘጸአት ተባለ። መጽሐፉ 40 ምዕራፎች ሲኖረው፡-

1. ከምዕ. 1-4 ሙሴ ከልደቱ ነፃ ለማውጣት እስከተጠራበት፤
2. ከምዕ. 5-11 በግብፅ የወረዱት 10 መቅሰፍታት፤
3. ከምዕ. 12-15 የኤርትራን ባህር በእግዚአብሔር ኃይል መሻገራቸው፤
4. ከምዕ. 16-40 የሙሴ በሲና ሕግን መቀበል፣ የእሥራኤል ጣኦት ማምለክ መቀጣትና መና እንደወረደላቸው እናገኛለን።

## ኦሪት ዘሌዋውያን

ሌዊ የሚባለው ከ12ቱ ነገደ እሥራኤል አንዱ ሲሆን በዘመነ ብሉይ የሌዊ ነገድ በአሮንና ልጆቹ መሪነት ወንድ ሁሉ ደብተራ ኦሪትን በክህነት የሚያገለግል ነበር። ዘሌዋውያን የተባለውም የሌዊን ነገድ የክህነት ሥርዓት ስለሚገልጽ ነው።

27 ምዕራፎች ሲኖሩትም ይዘቱም፦

1. ከምዕ. 1-10 ስለ መሥዋዕትና ሥርዓተ ክህነት፣
2. ከምዕ. 11-16 ስለ መባልዕትና መንጻት፣
3. ከምዕ. 17-22 ስለ ጋብቻና የህናት ምርጫ፣
4. ከምዕ. 23-27 ሕግና በዓላትን፣ በረከትንና መርገምን የሚገልጽ ሲሆን ሌሎችም ሕግጋተ እግዚአብሔር ተገልጸዋል።

## ኦሪት ዘኍልቍ

ዘኍልቍ ቆጠራ ማለት ሲሆን እሥራኤል፣ 1. በሲና ምድረ በዳ /1፥1-3/

2. በሞአብ /26፥1-4/ መቆጠራቸውን ስለሚገልጽ ዘኍልቍ ቆጠራ ይባላል። እሥራኤል ከግብፅ ከወጡ ከ2 ዓመት ከ1 ወር ጀምሮ ሞአብ ሜዳ ድረስ ያለውን ጉዞና እሥራኤል ባለመታዘዛቸው የደረሰባቸውን ጥፋት ይገልጻል። ከጥፋቶቹም፦

1. ምኞት /11፥4/ 2. ክፉ ወሬ /13፥14/ 3. የመሪባ ውኃ /20፥1/

በተጨማሪም የሙሴ እኅት ማርያምና አሮን ሞት፣ በመጨረሻም ምድረ ርስትን እንዴት እንደሚከፋፈሉ ሕግ ከእግዚአብሔር መሰጠቱን የሚገልጽ ሲሆን 36 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

## ኦሪት ዘዳግም

ዘዳግም ማለት የሚደገም ማለት ነው። በኦሪት ዘጸአት፣ ዘሌዋውያንና ዘኍልቍ የቀረቡትን ሕግጋትና ትእዛዛት በስብከት መልክ ስለሚደግማቸው ዘዳግም /የሚደገም/ ሲባል፣ መጽሐፉ 40 /አርባ/ ምዕራፎች አሉት።

ኦሪት ዘዳግም በዮርዳኖስ ማዶ ባሉት በሞአብ ምድር ሙሴ ለሕዝበ እሥራኤል የተናገረው ነው። ይህም እግዚአብሔር ስላደረገላቸውና ስለሰጣቸው ሕግ ማሳሰቢያ ከዚያም ሕጎችንና ደንቦችን እንደ አዲስ የሚተረጉም ሲሆን ሕግጋተ እግዚአብሔርን በመጠበቅ የሚገኝ በረከትና ባለመጠበቅ የሚመጣ መርገምን በምክር መልክ ያስረዳል።
በመጨረሻም፦ ኢያሱ ተሹሞ ሙሴ ዓርፎ ማረፉን ይገልጻል።

## መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ

በጸሐፊው ስም የተሰየመ መጽሐፍ ሲሆን፣ ኢያሱ አዳኝ ማለት ነው። የመጀመሪያ ስሙ "አውሴን" ይባል ነበር። ኢያሱ ያለው ሙሴ ነው። /ዘኁ. 13፥16/ ይህ መጽሐፍ ሃያ አራት ምዕራፎች ሲኖሩት ሦስቱ ዋና ትምህርቶችን ይዘዋል።

1. የእሥራኤልን ከነዓን መግባት
2. ምድረ ርስትን መከፋፈል
3. የኢያሱ የመጨረሻ ምክርና ዕረፍት

## መጽሐፈ መሳፍንት

መስፍን ፈራጅ አስተዳዳሪ ማለት ነው:: መጽሐፈ መሳፍንት የተባለበት ምክንያት ከኢያሱ ሞት በኋላ እስከ ሳኦል መንግሥ እሥራኤልን ያስተዳድሩ ስለነበሩ መሳፍንት ስለሚገልጽ ነው:: መጽሐፉን የጻፈው ሳሙኤል ነው ተብሎ በብዙ ሊቃውንት ይታመናል:: መጽሐፉ 21 ምዕራፎች አሉት:: እሥራኤል ከአምልኮተ እግዚአብሔር ሲርቁ ጣኦት ሲያመልኩ ለአሕዛብ ያስማርካቸው ነበር:: ተጸጸተው ሲመለሱም መሳፍንቱን እያስነሣ ነፃ ያወጣቸው ነበር:: /2÷11-23/

በዚህ ጊዜ የነበሩ መሳፍንት 15 ሲሆኑ በመጽሐፈ መሳፍንት የተጠቀሱት 13 ናቸው:: ያልተጠቀሱት ኤሊና ሳሙኤል የቤተመቅደስ ሊቃነ ካህናት ነበሩ:: እነዚህ መሳፍንት ለ45 ዓመታት አስተዳድረዋል:: /የሐዋ. ሥራ 13÷20/

- ⇨ በመጽሐፉ ክምዕ. 1-2 እሥራኤል የእግዚአብሔርን ውስታ መዘንጋታቸው፤
- ⇨ ክምዕ. 3-15 የመሳፍንቱ አነሳስና በነርሱ አማካይነት የተፈጸሙት ታሪኮች፤
- ⇨ ክምዕ 17-21 ንጉሥ ባልነበረበት ዘመን የተፈጸሙ ታሪኮችን እናገኛለን::

## መጽሐፈ ሩት

መጽሐፉ በነቢዩ ሳሙኤል እንደተጻፈ የሚታመን ሲሆን 4 ምዕራፎች አሉት:: በዘመነ መሳፍንት አቤሜሌክና ኑሐሚን ከሁለት ወንድ ልጆቻቸው ጋር በረሃብ ከቤተልሔም ዘይሁዳ ወደ ሞአብ መሰደዳቸውና በቤተሰቡ የደረሰው መከራ እንዲሁም ሞዓባዊቷ ሩት ለኑኃሚን ያደረገችላትን ውለታና ሩት የንጉሥ ዳዊት ቅድመ አያት መሆኗን ይገልጻል::

- ⇨ በምዕ. 1 መሰደዳቸውና ክስደት መልስ፤
- ⇨ ክምዕ. 2-3 ሩት የቦኤዝን እርሻ በመቃረም ኑኃሚንን መርዳቷና፤
- ⇨ በምዕ. 4 ቦኤዝን አግብታ በዳዊት ሐረግ መቆጠሯን እናገኛለን::

## መጽሐፈ ኩፋሌ

ኩፋሌ መክፈል ማለት ሲሆን ክአራት የተከፈለ ማለት ነው:: በመጀመሪያው የሥነ ፍጥረት ቀን ጀምሮ እሥራኤል ከግብፅ እስከወጡበት ድረስ ያለውን በአራት መጻሕፍት የተጠቀሰ ታሪክ የሚገልጹ 34 ምዕራፎች ያሉት በሙሴ የተጻፈ መጽሐፍ ነው::

መጽሐፉ:-

1. ከአዳም እስከ ሙሴ ያለውን /3830 ዓመት/ ታሪክ ይተርካል፤
2. ታሪኮቹ የተፈጸሙበትን ዘመናት በሱባኤ ይገልጻል፤
3. ታሪኩን ከሕግ ጋር እያዛመደ ያስረዳል:: ለምሳሌ:- አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩበት ምድር ወደ ገነት የገቡበት በ40 እና በ80 ቀናቸው እንደሆነ በምዕ. 4÷8-13 ሲገልጽ ይህም በዘፍ. 27-25 ካለው ታሪክና ዘሌ. 12÷1-5 ከተሰጠው ሕግ ጋር አዛምዶ የተፈጸመባቸው ጊዜያት በሱባዔ ቆጥሮ ይገልጻል::

## መጽሐፈ ሄኖክ

መጽሐፈ ሄኖክ እንደ ቤተክርስቲያናችን አቆጣጠር በ4014 ዓ.ዓ. ከጌታ ልደት በፊት ሄኖክ እንደጻፈው ይታመናል። እንዲሁም ሐዋርያት የገለጹት /ይሁዳ 1÷14-70/ ሊቃውንትም የተረጎሙት ሲሆን:-

1/ ስለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
2/ ስለፀሐይ፣ ጨረቃ ሁዳትና ስለ እፅዋት
3/ ስለ ቅዱሳን መላእክት
4/ ስለ ጻድቃንና ኃጥአን
5/ በኖኅ ዘመን የተፈጸመው ኃጢአትና ቅጣትን በሰፊው የሚገልጽ 42 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

# የታሪክ ክፍል መጻሕፍት

## 1. መጽሐፈ ዮዲት

16 ምዕራፎች ያሉት በእግዚአብሔር ጥበብ ሆሊፍርኒስ የተባለውን የናቡከደነጾር የጦሪ መሪ ገድላ ወገኖቿን እና ሀገሯን እንዴት እንዳዳነች የሚገልጽ መጽሐፍ መሳ. 3÷15-30 ከተጠቀሰው የናኦድ ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ታሪክ ነው። በማንና መቼ? እንደተጻፈ በትክክል ባይታወቅም በስደት የነበሩ አይሁድ ሳይጽፉ አይቀርም። ታሪኩ የተፈጸመው 600 /ስድስት መቶ/ ዓመታት ከጌታ ልደት በፊት ሲሆን መጽሐፉ:-

ሀ. በሆሊፍርኒስ የጦር ዘመቻና የእሥራኤል ልደት ፍርሐት /ከምዕ. 1÷7/፤
ለ. ዮዲት ሆሊፍርኒስን ገድላ ወገኖቿን ማዳኗ /ምዕ. 8÷15/ እናገኛለን፤
ሐ. ዮዲት ለእግዚአብሔር ያቀረበችው ምስጋና እና እረፍቷን /በምዕ. 16/ እናገኛለን።

## 2. መጽሐፈ ነገሥት /መጽሐፈ ሳሙኤል/ ቀዳማዊ እና ካልዕ

እነዚህ መጻሕፍት በነቢዩ ሳሙኤል የተጠሩት ሳሙኤል ስለጀመራቸው ሲሆን 1ኛ ሳሙኤልን የተወሰነውን ክፍል፤ 2ኛ ሳሙኤልን ናታንና ጋድ ጽፈውታል /1ኛ ዜና መዋ. 29÷29/

### መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ

ስለነቢዩ ሳሙኤል አጠራር፣ የታቦተ ጽዮን መማረክና ኃይል አድርጎ መመለስ፣ የመጀመሪያው የእሥራኤል ንጉሥ ሳኦል መንግሥትና የዳዊት በሳኦል መተካትን ይገልጻል።

### መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ

ሙሉ በሙሉ የዳዊትን ታሪክ ሲገልጽ፤ ዳዊት ምንም እንኳን ልበ አምላክ ቢባልም ሁለት ጊዜ እግዚአብሔርን እንደ አሳዘነና በንስሐ በመመለሱም እግዚአብሔር እንደተደሰተበት፣

ለቃል ኪዳኑ ታቦት የነበረውንም ክብር እናያለን። በአጠቃላይ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል በአራት ዐበይት ጉዳዮች ይካተታል። እነርሱም፦

1. የነሳሙኤል ሕይወት
2. የሳኦል ዘመነ መንግሥት
3. የታቦተ ጽዮን ክብር
4. የዳዊት ዘመነ መንግሥት

## 2. መጽሐፈ ነገሥት /መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ/ ሣልስና ራብዕ

እነዚህ ሁለት መጻሕፍት ከሰሎሞን እስከ ይሁዳ በባቢሎን መማረክ ያለውን የሁለቱን /የእስራኤልና ይሁዳ/ ነገሥታትና ሕዝብ ታሪክ ሲገልጹ በመጻሕፍቱ በአጠቃላይ የሚከተሉትን ይገልጻሉ፦

1. የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት
2. የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት
3. የእግዚአብሔር ነቢያት ታሪክ ሲሆን 1ኛ ነገሥት 22፣ 2ኛ ነገሥት 25 ምዕራፎች አሉት።

ሁለቱ መጻሕፍት /ከ1ኛ ሳሙኤል 2ኛ ሳሙኤል መጽ. ነገሥት /700/ ሰባት መቶ/ ዓመታት ታሪክ ሲይዙ በፍትሐ ነገሥት 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል መጽ.ነገ. 1ኛና 2ኛ፤ መጽ. ነገሥት 1ኛ እና 2ኛ ደግሞ 3ኛ እና 4ኛ ነገሥት ይባላሉ።

አሁን ባለው መልኩ የተጻፈውም 70 የአይሁድ ሊቃውንት የቀዱሳት መጻሕፍትን ወደ ግሪክ ከተረጎሙ በኋላ ሲሆን በፊት ግን ከፍትሐ ነገሥት እንደተገለጸው ነበር።

### መጽሐፈ ዜና መዋዕል

ዜና መዋዕል የዕለት ዜና /ድርጊት/ ማለት ነው። ከመጽሐፈ ነገሥት ጋር ተመሳሳይ መጽሐፍ ሲሆን ልዩ የሚያደርገው ለመንፈሳዊ ጉዳዮች ትኩረት መስጠቱ ነው፤ በነቢዩና ካህኑ ዕዝራ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ 500 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት በአንድ ላይ ቀጽፎ በ70 ሊቃውንት ለሁለት ተከፍሏል።

### 3. ዜና መዋዕል ቀዳማዊ

1. ከአዳም እስከ ሳኦል የነበሩትን አባቶች ትውልድና አጭር ታሪክ /ከምዕራፍ 1-10/፤
2. የንጉሥ ዳዊትን ታሪክ ብቻስይ መንፈሳዊ ተግባራቱን /ከምዕራፍ 11-29/ የሚገልጽ 29 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

### 4. ዜና መዋዕል ካልዕ

36 ምዕራፎች ያሉት ከዜና መዋዕል ቀዳማዊ የሚቀጥል፤ ከሰሎሞን በሴዴቅያስ ዘመን ኢየሩሳሌም በባቢሎን እስከተማረከችበት ያለውን ታሪክ እናገኛለን። መፍቀሬ እግዚአብሔር ስለነበሩ የይሁዳ ነገሥታት ታሪክም በሰፊው ይገልጻል።

### የምናሴ ጸሎት

በዜና መዋዕል ካልዕ 33፥13 እንደተገለጸው፤ ምናሴ በተጨነቀ ጊዜ የጸለየው 13፥1 ምዕራፍ ያለው፤ ከዜና መዋዕል ካልዕ ጋር የሚቆጠር የጸሎት መጽሐፍ ነው።

### 5. መጽሐፈ ዕዝራ

በባቢሎን የ70 ዓመት ምርኮ የነበረውን ታሪክ የሚገልጽ 10 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ሲሆን፦

1.ንጉሡ ፋርስቁርስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ቤተ መቅደስ እንዲያድሱ ማዘዙ፣ በዘሩባቤል መሪነት ተመልሰው መሥራታቸው /ከም.ዕ 1÷6/

2.የቀሩት በዕዝራ መሪነት ተመልሰው ሥርዓት ማስተካከላቸውን /ከም.7÷10/ ይገልጻል።

## መጽሐፈ ነህምያ

በግዕዝ የመጽሐፈ ዕዝራ ከፍልቀየህምያዕዝራ የቲጸሔ 13 ምዕራፎች ያሉት፦

1. ነህምያ በእግዚአብሔር ቸርነት በኢየሩሳሌም ቅጥርዋን መሥራቱን /ከምዕ. 1-7/ ጸሎት ማድረጋቸው /ከምዕ. 8-10/፣
2. በዕዝራ የሙሴ ሕግ መነበቡ፣ ሕዝቡም የዳስ በዓሉን አክብረው የንስሐ ጾምና ጸሎትም ማድረጋቸው /ከምዕ. 8-10/፣
3. ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ ዕጣ ተጣጥለው በምድሪቱ መሥፈራቸውንና የነህምያ ተግሳጽ/ከምዕ. 11-13/።

## 6. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል

ሱቱኤል የጸሐፊው የዕዝራ ድርብ ስም ሲሆን፤ 13 ምዕራፎች ያሉት ዕዝራ በተማረከበት ሀገር በባቢሎን ስላያቸው ራዕዮች እንዲሁም ላቀረባቸው ጥያቄዎች በምሳሌ የተሰጠውን መልስ እና በመጨረሻም ዕዝራ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቆ ልዩ መንፈሳዊ ፀጋና ዕውቀት ተሰጥቶት ከ40 ቀናት በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደጻፈ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው።

## መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

ዘጠኝ ምዕራፎች ያሉት የዕዝራ መጽሐፍ ሲሆን፣

1. በዜና መዋዕል ካልዕ ከምዕ. 35-36 የተገለጸውን በምዕ.1፤
2. በመጽሐፈ ዕዝራ የተገለጸውን ከምዕ. 2-9፤
3. በመጽሐፈ ነህምያ ከምዕ. 7-8 የተገለጸውን ታሪክ በስፋት የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። ይህም መጽሐፈ ነገሥት የተገለጸው በዜና መዋዕል በድጋሚ እንደተገለጸው ዓይነት ነው።

## 7. መጽሐፈ አስቴር

በትልቁ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት በአስቴር የተሰየሙ መጻሕፍት ሲኖሩ፤ በ66ቱ ቁጥር የሚገኘውን በቅድሚያ እናያለን።

ይሄህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ስም ያልተጠቀሰ ሲሆን፤ በ127 አገሮች ንግሥ በነበረው በአርጤክስ ዘመን የተፈጸመ ታሪክ የሚገልጽ 10 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው። በይዘቱም፦

1. ንጉሥ አርጤክስ አስቴርን ማግባቱንና መርዶክዮስ በንጉሡ የታቀደውን ግድያ ማጋለጡ /ከምዕ. 1-2/፤
2. ሐማ በመርዶክዮስና በአይሁድ ያሴረው ሤራ /ከምዕ. 3-5/፤
3. በአስቴር አማካይነት አይሁድ ሦስት ቀን ከጾሙ በኋላ ሐማ እና የአይሁድ ጠላቶች መጥፋታቸው /ከምዕ.6-10/ ይገልጻል። ሁለተኛው /በ81 ዱ መጽሐፍ ጥራዝ ብቻ የሚገኘው/

መጽሐፈ አስቴር፦ 11 ምዕራፎች ይዞ ከላይ ባየነው መሠረት ያሉትን በስፋት የሚገልጽ የሚደግም ነው። ከላይኛው የሚለየውም የታሪኩ መነሻ ሕልም ከነትርጓሜው በመጽሐፉ በመጀመሪያና መጨረሻ ስለሚገልጽ ሲሆን፤ በተጨማሪም በዚህኛው መጽሐፈ አስቴር

የእግዚአብሔር ስም ተጠቅሷል። መጽሐፈ አስቴርን ማን እንደጻፈው በትክክል ባይታወቅም የፋርስን ቤተመንግሥት ሥርዓት የሚያውቅ መርዶክዮስ እንደጻፈው በብዙ ሊቃውንት ይታመናል።

<u>መጻሕፍተ መቃብያን</u>፡ በዓለም ስምንት የሚደርሱ የመቃብያን መጻሕፍት አሉ። ማን እንደጻፋቸው በግልጽ አይታወቅም። ከነዚህም ሁለቱ በፍትሐ ነገሥት የተገለጹት የሚከተሉት ናቸው።

## 8. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ

16 ምዕራፎች የያዘ ይሁዳ መቃብያስንና ወንድሞቹ ሃይማኖታዊ ሕግና ሥርዓት ለመጠበቅ ከሌሎች መንግሥታት ጋር ያደረጉትን ተጋድሎ ይገልጻል።

## 9. መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ

በ15 ምዕራፎች የተከፈለ የመጀመሪያው ትክታይና በተለይም በግብጽ የሚኖሩ አይሁድ በኢየሩሳሌም ቤተመቅደሱ ይፈርሳል ብለው ስለሚፈሩት አደጋ ይዘረዝራል። እነዚህ ከላይ ያየናቸው የመቃብያን መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት የመቃብያን መጻሕፍት ይለያል። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትም፡-

### 1. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ

የመቃቢስ ዘብንያም ልጆች አብያ፣ ሲሳስና ፊንቶስ ከሁለት ወንድሞቻቸው ጋር የተቀበሉትን ሰማዕትነት የተናገሩትን እንዲሁም ከብሉይ ኪዳን ታሪኮችና ምሳሌዎችን እየጠቀሱ ስለትንሣኤ ሙታን፣ የሰው ልጅ የነፍስና ሥጋ በረከትና ሕይወት ስለሚያገኝበት መንገድ የመከሩትን ሲገልጽ፣ በተጨማሪም ይሁዳ፣ መብክዩስና መቃቢስ 36 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

### 2. መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ፡- 21 ምዕራፎች አሉት።

- ሀ. ከምዕራፍ 1-4 መቃቢስ ዘሞዓብ የተባለው ንጉሥ በኢየሩሳሌም ያደረሰው ጥፋት፣ በንስሐ ተመልሶ የሠራውን በጎ ሥራና ዕረፍቱን፣
- ለ. ከምዕራፍ 5-12 የመቃቢስ ዘሞዓብ ልጆች በእግዚአብሔር ስላመኑ ጺሩጻይዳን የተባለው የከለዳውያን ንጉሥ ያደረሰባቸው መከራ፤
- ሐ. ከምዕራፍ 13-21 የመቃቢስ ዘሞዓብ ልጆችን አብነት አድርጎ ስለትንሣኤ ሙታን ለማያምኑ የተሰጠ መልስ የያዘ መጽሐፍ ነው።

### 3. መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ

የብሉይ ኪዳንን ታሪኮች እየጠቀሰ የጽድቅና የኩነኔን የትንሣኤ ሙታንን እንዲሁም ዲያቢሎስ የሰው ልጆችን የሚያስትባቸውን መረቦች የሚገልጽ 10 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

## 10. መጽሐፈ ጦቢት

የቅዱሳት መላእክት ተራዳኢነት ስለተደረገለት ጦቢት ስለተባለው ቅዱስ አባትና ቤተሰቡ የሚገልጽ 14 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

1. ጦቢት በበጎ ሥራው እያለ ባገኘው መከራ እና ሣራ የተባለችው ሴት የጸለዩት ጸሎት /ከምዕ. 1-3/፤
2. ጦቢት በመከራው ጊዜ ልጁን ጦቢያን ወደ ወገኖቹ ሲልክ ቅዱስ ሩፋኤል በሰው ተመስሎ እንዴት እንደረዳቸው /ከምዕ. 4-12/፤

3. ጦቢት /ከምዕራፍ 13-14/ መጽሐፉ ከ700ኛው -500ኛው ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የተፈጸመውን ታሪክ ይገልጻል።

## የመዝሙር ክፍል መጻሕፍት

**መዝሙር**፡- ማዜም ማለት ነው። በዚህ ትምህርታችንም ይህንን መዝሙርን የያዙትንና በመዝሙር መልክ የተጻፉ ታሪካዊና የጥበብ /የምክር/ መጻሕፍትን እናገኛለን።

### 1. መጽሐፈ ኢዮብ

ዖጽ በሚባል ሀገር ስለነበረ ኢዮብ ስለተባለ ጻድቅ በዲያብሎስ ተንኮል በእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈትኖ በትእግስት ማለፉን የሚገልጽ 42 ምዕራፎች ያሉት አጻጻፉም ከመጀመሪያውና ከመጨረሻው በስተቀር እንደ መዝሙር ምሳሌ ዓይነት አጻጻፍ ያለ መጽሐፍ ሲሆን፤

ሀ. የኢዮብ መፈተን /ከምዕራፍ 1-3/፤

ለ. ጓደኞቹ እንደተከራከሩት /ከምዕራፍ 4-37/፤

ሐ. የእግዚአብሔር ጥያቄና የኢዮብ አጥፍ በረከት መቀበል /ምዕራ. 39-42/።

ኢዮብ በመሥዋዕት አቀራረቡ ከአብርሃም አምስተኛ ትውልድ ለሙሴ ሕግ ከመሰጠቱ በፊት የነበረ እንደሆነ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ያስረዳሉ።

### 2. መዝሙረ ዳዊት

150 መዝሙራትን የያዘ በቤተክርስቲያናችን ሆነ በሌሎች ዘንድ ተወዳጅነት ያለው መጽሐፍ ሲሆን የቤተክርስቲያናችን የጸሎት፣ የመዝሙር መጻሕፍትም መሠረታቸው ይህ መጽሐፍ ነው። /ስምዓሴ ድጓ/

መዝሙራትን ማን እንዳሰባሰበው ባይታወቅም ንጉሥ ዳዊት በነበረበት ዘመን ጀምሮ ታል /1ኛ ዜና 16/። ነገር ግን ከምርኮ በኋላ ስለነበሩ ሁኔታዎች የሚገልጽ ዕዝራ አሰባሰቦ በአሁኑ መልክ ሳያዘጋጀው አልቀረም የሚሉ ሲኖሩ በቤተክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጎ የሚሰጠው አንድምታዊ ትምህርት የሚከተለው ነው።

**ዳዊት ልበ አምላክ**፡- የተመረጠ ማለት ሲሆን የመጀመሪያው ንጉሥ ሳኦል ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ፣ ዳዊትን በነቢዩ ሳሙኤል አማካኝነት እግዚአብሔር ለንግሥና መረጠና ቀባው። ሲቀባውም ለዳዊት ሰባቱ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ተሰጥተውታል። እነዚህም፡-

| | | |
|---|---|---|
| 1. ሀብተ መንግሥት | 4. ሀብተ መዊዕ /ማሸነፍ/ | 7. ሀብተ ትንቢት |
| 2. ሀብተ ክህነት | 5. ሀብተ በገና | ናቸው። |
| 3. ሀብተ ኃይል | 6. ሀብተ ፈውስ | |

ሀብተ ትንቢትም 150 መዝሙራትን መድረስ ትንቢትን መናገር ነው። እነዚህም /ዳዊት በተሰጠው ፀጋ የደረሳቸው መዝሙራት/ የዳዊት መዝሙራት ሲባሉ በአሥር አርዕስት ይከፈላሉ። እነርሱም፡-

1. ስሁሉም ተግሳፅ /ምክር/ መዝ. 1÷1
2. ስለክርስቶስ የተነገረ /መዝ. 2÷1/
3. ስለዳዊት የተነገረ /መዝ. 3÷1/

4. ስለመናንያን የተነገረ /መዝ. 4፥1/
5. ስለትሩፋት የተነገረ /መዝ. 5፥1/
6. ስለ ሕዝቅያስ የተነገረ /መዝ. 13፥1/
7. ስለኤርምያስ የተነገረ /መዝ. 34፥1/
8. ስለመቃብያን የተነገረ /መዝ. 43፥1/
9. ለካህናት ተግሣጽ /መዝ. 49፥1/
10. ስለ ሰሎሞን /መዝ. 71፥1/ የተነገሩ ትንቢቶችና ሌሎች 140 በእነዚህ ሥር ይካተታሉ።

በዚህም 7 ዓበይት ትምህርት የሚሰጡ ነገሮች አሉበት።

እነርሱም፦ 1. ጠላትን መውደድ /16፥4/ 2. ትህትና /21፥6/
3. ሃይማኖት /21፥10/ 4. ትስፋ መንግሥተ ሰማያት /26፥1/
5. ኃጢአትን ማመን /37፥4/ 6. ይቅርታን /50/
7. ምፅዋት /111፥8/ ናቸው።

ስለዚህም መዝሙረ ዳዊት ከዳዊት በፊትም ሆነ በኋላ የተደረጉትን ድርጊቶች መግለጻቸው ያለፈውን አንስቶ ምክር ተግሳጽና ምስጋና ለወደፊት ስለሚሆነው በትንቢት መናገር ነው። በአጠቃላይ መዝሙረ ዳዊት ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመት በንጉሥ ዳዊት የተጻፈ ለሀዘን፣ ለደስታ፣ ለምክር፣ ለመጽናናት፣ ለሁሉም የሚሆን መጽሐፍ ነው።

## 3. መጽሐፈ ምሳሌ

የሰው ሕይወት በየክፍሉ /በማኅበራዊና በሃይማኖት/ ተገቢውን አካሄድ በምሳሌ አድርጎ ትምህርትና ምክር የሚሰጥ 24 ምዕራፎች ያሉት እንደ ታሪክና መዝሙር ያልተያያዘ በዳዊት ልጅ በሰሎሞን የተጻፈ ሲሆን፦

1. ስለ ጥበብና መማር ማወቅ እንደሚጠቅም /ከምዕ. 1፥9/
2. በእያንዳንዱ መስመር ልብን ለማደስ ሥነ ምግባርን ለማጎልመስ የሚረዱ ምክሮች /ከምዕ. 10-22/
3. ጥበብን ለማግኘት የሚቻልባቸውን የሚሰጥ /ከምዕራፍ 22፥17-24/ መጽሐፍ ነው።

## 4. መጽሐፈ ተግሳጽ

7 ምዕራፎች ያሉት ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይ አቀራረብ ያለው ሲሆን በንጉሥ ሰሎሞን፣ በአጉርና ልሙኤል የተነገሩ፣ በይሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስ ዘመን በጸሐፍት የተሰበሰቡ ናቸው። /ተግሳጽ 1፥1/ 6፥1፣ 7፥1 ወይም ምሳሌ 25፥1 /30፥1/ 31፥1 በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ጥራዝ /ተግሳጽ/ ተብሎ በመጽሐፈ ምሳሌ ከምዕ. 25-31 በድርብ የሚገኝ ሲሆን በግዕዙ ግን ራሱን ችሎ መጽሐፈ ተግሳፅ ይባላል።

1. ከምዕ. 1-5 የንጉሥ ሰሎሞን ምሳሌዎች፤
2. ከምዕ. 6 የማሣ አገር ሰው ለኢትኤልና ለኡክል የተናገረው፤
3. የማሣ ንጉሥ የልሙኤል ቃል /በምዕ. 7/ እናገኛለን።

### 5. መጽሐፈ ጥበብ

እንደ መጽሐፈ ምሳሌ ተመሳሳይ ሐሳብ ያለው በ19 ምዕራፎች የተከፋፈለ፤ የንጉሥ ሰሎሞን መጽሐፍ ነው:: /ጥበብ 9-7/ 1ኛ ነገ.9÷11 በተለይም ስለ ጥበብ ጥቅም በመምከር ሰው ጥበብን እንዲፈልግ ይመክራል::

### 6. መጽሐፈ መክብብ

መክብብ ሰባኪ፣ አስተማሪ /ሹም/ ማለት ሲሆን፤ መጽሐፉ 12 ምዕራፎች ያሉት ነው:: የሰውን ተፈጥሮ፣ የሥራውንና የዓለምን ከንቱነትና አዲስ ነገር እንደሌለ ይገልጻል:: ትምህርቱን በማጽናት የጭንቅና የሕይወት ፍጻሜ ጊዜ ሳይደርስ፤ በዓለም አጥጋቢ፣ ዘለቄታ ያለው ደስታ ስለማይገኝ ሁሉም ከንቱ ስለሆነ ፈጣሪህን አስብ በማለት ከራሱ ሕይወት በመነሳት ያስተምራል:: እንዲሁም በመጽሐፈ ጥበብ ባኅር ይባላል:: "ባኅር" ማለትም የንጉሥ ሰሎሞን የፍልስፍና ስም ነው::

### 7. መኃልዬ መኃልይ ዘሰሎሞን

ከመዝሙራት የሚበልጥ የሰሎሞን መዝሙር ማለት ሲሆን 8 ምዕራፎች ያሉት የሰሎሞን መጽሐፍ ነው:: በይዘቱም ቅዱስ ጳውሎስ የቤተክርስቲያንና የክርስቶስን ምሥጢር ለባልና ሚስት አድርጎ በምዕ. 5÷31-32 እንደገለጸው፣ ሰሎሞንም በወንድና ሴት ፍቅረኞች ምሳሌ:- የእግዚአብሔርና የእሥራኤል፣ የክርስቶስንና ስለጠፋው የሰው ልጅ /የክርስቶስንና የቤተክርስቲያንን/ ፍቅር መጠን ይገልጻል:: /ሆሴዕ 1÷9፣ ኢሳ.54÷1፣ ሕዝ.16÷1፣ ዮሐ.3÷27-29፣ ኤፌ 5÷31-32/ የእሥራኤል ቆነጃጅትም . . . እያለ ቅዱሳን መላእክትን/ ነቢያትንና መምህራንን ይጠቅሳል::

በአጠቃላይ ሰሎሞን 5 መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ሲኖሩት እንዲሁም 3000 ምሳሌዎች 1005 መኃልይም ነበረው /1ኛ ነገ. 4÷32/::

### 8. መጽሐፈ ሲራክ

በሲራክ ተጽፎ በልጅ ልጅ ወደ ግሪክ የተተረጐመ 51 ምዕራፎችን የሰሎሞንን ምሳሌዎች የሚመስል ለመንፈሳዊ ሥጋና ሕይወት ጥበብና ምክር የሚሰጥ መጽሐፍ ነው:: ሲራክ ከጌታ ልደት 180 ዓመት በፊት የነበረ ሲሆን መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥበብ እግዚአብሔርን ለምኖ ተገልጾለት የጻፈው ነው::

## የትንቢት ክፍል

ነቢያት ወደፊት የሚደረገውን የሚተነብዩ ሲሆኑ የተነበዩት /የተናገሩት/ ደግሞ ትንቢት ይባላል:: ነብያት የቃልና የጽሑፍ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ::

ሀ/ የቃል:- የተናገሩትን ትንቢት በጽሑፍ ያላሠፈሩ የተነገራቸውን በታሪክ መጻሕፍት የተጻፉ ናቸው::

ለምሳሌ :- ኤልያስ፣ ኤልሳዕ፣ ረዓይ፣ አኪይ ወዘተ

ለ/ የጽሑፍ:- የተናገሩትን በጽሑፍ ያሠፈሩ ናቸው:: እነዚህም በጻፏቸው መጻሕፍት ምዕራፍና ቁጥር ብዛት በማዕረጋቸው /ብቃታቸው/ ዐበይትና ደቂቅ ተብለው ይከፈላሉ::

1. ዐበይት:- የሚባሉት ኢሳይያስ፣ ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤልና ዳንኤል ሲሆኑ
2. ደቂቅ:- ነቢያትም ከትንቢተ ሆሴዕ እስከ ሚልክያስ ያሉት ስማቸው በመጻሕፍቶቻቸው በርዕስነት የተጠቀሱት ናቸው::

## 1. ትንቢተ ኢሳይያስ

ኢሳይያስ መድኃኒት ማለት ሲሆን መጽሐፉ 66 ምዕራፎች ያሉት ከጌታ ልደት በፊት 700 ዓ.ም. የተጻፈ ነው። ነቢዩ በትንቢቱ፦

ሀ. ስለ ባቢሎን ምርኮ፤

ለ. ከምርኮ ስለመመለሳቸውና፤

ሐ. ስለጽዮን /በተለየየ መልኩ/ የሚናገር ሲሆን በተለይም ስለጌታችን ግልጽ ትንቢቶችን ተናግሯል። /7፥14፤ 5፥31፤ 9፥6/ በዚህም የውጭ ሊቃውንት ወንጌላዊ ነቢይ የሀገራችን ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ደግሞ ደረቅ ሐዋስ ይሉታል።

ነቢዩ ኢሳይያስ ሕዝያን ክህነት ሳይኖረው ቤተ መቅደስ ሲያጥን ባለመገሰጹ ለ3 ዓመት ነቢይነት ከተነሣ በኋላ በትንቢተ ኢሳ. 6፥1 እንደምናገኘው በድጋሚ የተነሳ ታላቅ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው።

## 2. ትንቢተ ኤርሚያስ

ኤርሚያስ እግዚአብሔር ከፍ ያደርጋል ማለት ነው። ከጌታ ልደት በፊት በ600 ዓ.ም. በባቢሎን ምርኮ የነበረ ካህን ሲሆን የመከራ፣ የልቅሶ፣ የሰቆቃ ነቢይ ይባላል። ከማኅፀን የተመረጠ በ20 ዓመቱ የተጠራ /1፥4-7/ በመጨረሻም በድንጋይ ተወግሮ በሰማዕትነት ያረፈ በሕይወቱም ስለ እግዚአብሔር ቃል እየመሠከረ ብዙ መከራ የተቀበለ ነቢይ ነው። /ተረፈ ኤር. 11፥61/ መጽሐፉ 52 ምዕራፎች ያሉት ስለ ኢየሩሳሌም ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት ሀገሮችም የተነበየ፣ በተለይም ስለ ባቢሎን ምርኮ የሕዝቡን በደል እየነገረ እንዲመለሱ በትንቢት ያስጠነቅቃል። የኢየሩሳሌምን በባቢሎን መማረክ ይገልጻል። በተጨማሪም ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር የሚቆጠሩ 1. በነቢዩ 2. በደቀመዝሙሩ በባሮክ የተጻፉ መጻሕፍት አሉ። እነዚህም፦

1. <u>ሰቆቃው ኤርምያስ</u>፦ ሰቆቃ ልቅሶ፣ ሙሾ ማለት ነው። /ተረፈ ኤር.8፥22፣ 2ኛ ዜና 35፥25/ ነቢዩ ኤርምያስ በኢዮስያስ ማለት በኢየሩሳሌም መጥፋት ያለቀሰውን የጻፈው 5 ምዕራፍ ያለው መጽሐፍ ነው።
2. <u>ተረፈ ኤርምያስ</u>፦ ከሰቆቃው ኤርምያስ ቀጥሎ ምዕራፍ 6 ብሎ የሚጀምር 6 ምዕራፎች ያሉት ስለ ባቢሎን ምርኮ /ስለ ኤርምያስ/ ለባሮክና ለአቤሜሌክ የምርኮውን ዘመን እግዚአብሔር እንዴት እንዳሳለፋቸው፣ በነቢዩ ኤርምያስ ስለተመለሱ ምርኮዎችና ስለ ኤርምያስ ሰማዕትነት የሚገልጽ በባሮክ የተጻፈ መጽሐፍ ነው። /ተረፈ ኤርምያስ 11፥63/
3. <u>መጽሐፈ ባሮክ</u>፦ በባቢሎን ለተማረኩት አይሁድ የላከላቸው 5 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው። በይዘቱም አይሁድን ለንስሐ የሚቀሰቅስ ጸሎት ምክር እናገኛለን። ከላይ ያየናቸው ሦስት መጻሕፍት የተጻፉበት ጊዜ ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር ተቀራራቢ ነው።

## 3. ትንቢተ ሕዝቅኤል

ሕዝቅኤል እግዚአብሔር ብርታት ይሰጣል ማለት ሲሆን፤ 600 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረና በልጅነት ወደ ባቢሎን የተማረከ እዚያው ለ20 ዓመታት እያስተማረ ቆይቶ በሰማዕትነት ያረፈ ነው። መጽሐፉ 48 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን፦

ሀ. የእግዚአብሔርን ቃል ማስተላለፍ ስላለበት ኃላፊነት፣ ስለ አይሁድ በባቢሎን መማረክ /ከም. 1-24/፤

ለ. ከምርኮ መመለሳቸው፣ ቤተመቅደስ መታደስ፣ የሕንፃው አሠራር፣ ምድረ ርስት ክፍፍል፣ ስለ መንግሥተ ሰማያት /ከም. 25-48/ በተጨማሪም ሕዝቅኤል ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ /43፥1-2/ ስለ

እመቤታችን /44፥2/ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት /36፥25-27/ ስለ ትንሣኤ ሙታን /37፥1/ የጻፈ ሲሆን እንዲሁም ሕዝቅኤል እንደ ትንቢተ ኢሳይያስና ተረፈ ኤርምያስ ግልጽ ትንቢት ያለው መጽሐፍ ነበረው፤ አቃጥለውታል::

## 4. ትንቢተ ዳንኤል

ዳንኤል እግዚአብሔር ፈራጅ ነው ማለት ሲሆን፤ ከጌታ ልደት በፊት 600 ዓመት ናቡከደነጾር /ብልጣሶር/ በቂርስን ዳርዮስ ዘመን የሕዝቅኤል ጓደኛ የነበረ ነቢይ ነው፤ መጽሐፉም በ12 ምዕራፎች የተከፈለ ነው:: 1. የነቢዩ ዳንኤልና የ3ቱ ደቂቅ /አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል/ በናቡከደነጾር ቤተ መንግሥት መመረጥ ነው:: 2. የነቢዩ ዳንኤል የሕልም ትርጉም አዋቂነትና 3. ለነቢዩ ዳንኤል የተገለጸለት ምሥጢር /ስለጌታችን ዳግም ምጽአት፣ በምድር ስለሚፈጸሙ ታሪኮችን ወ.ዘ.ተ. የምናገኝበት መጽሐፍ ሲሆን፣ በተጨማሪም ነቢዩ ከዚሁ ጋር የሚቀጠሩ 3 መጻሕፍት አሉት:: እነርሱም:-

### 4.1 ጸሎተ 3ቱ ደቂቅ /የሦስቱ ልጆች መዝሙር/

በትንቢተ ዳንኤል 3፥23 ባለው ታሪክ መሠረት ሠለስቱ ደቂቅ ሲድራቅ፣ ሚሳቅ አብደናጎም /አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል/ ታሥረው በሚነድ እሳት በተጣሉ ጊዜ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ያቀረቡትን ጸሎትና ምስጋና የሚገልጽ አንድ ምዕራፍ ያለው መጽሐፍ ነው::

### 4.2 ታሪክ ሶስና

ሶስና በዝሙት ወንጀል ተፈርዶባት ልትወገር ስትል ነቢዩ ዳንኤል የእግዚአብሔር ጥበብ በሞላበት ዘዴና ፍርድ እንደአዳናት የሚገልጽ አንድ ምዕራፍ ያለው መጽሐፍ ነው::

### 4.3 ተረፈ ዳንኤል

ይህ መጽሐፍ አንድ ምዕራፍ ያለው:-

ሀ. ፈሪሳውያን የባቢሎን ሰዎች ያመልኳቸው የነበሩትን ጣዖት ነቢዩ ዳንኤል እንዴት እንዳጠፋና እንዳሳፈረ /ከቁ. 1-28/፤

ለ. ነቢዩ ዳንኤልን እግዚአብሔር ከአንበሶች አፍ እንዳዳነው /ከቁ. 29-42/ የሚገልጽ ከት.ዳንኤል 6፥4-24 ላይ ከተጠቀሰው ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያለውና አስፍቶ የሚገልጽ ነው::

## 5. ትንቢተ ሆሴዕ

ሆሴዕ እግዚአብሔር ያድናል ማለት ሲሆን፤ በ700 ዓ.ም. /ከጌታ ልደት በፊት የነበረ የእሥራኤል ነቢይ ነው:: ትንቢተ ሆሴዕ 14 ምዕራፎች ሲኖሩት ስለ እግዚአብሔርና ሕዝበ እሥራኤል፤ በነቢዩ፣ በሚስቱና ከልጆቹም ምሳሌ እያደረገ /ሆኖ/ ያስተማረና የተነበየ ነው:: ሆሴዕ ስለጌታችን በምዕ. 61፥3-17 ተንብዮአል::

## 6. ትንቢተ አሞጽ

አሞጽ ከእረኝነት የተጠራ የእሥራኤል ነቢይ ነው:: 7፥14 በዘጠኝ ምዕራፎች የከፈለው መጽሐፉ:-

ሀ. የፍልስጥኤም እሥራኤል ሕዝብ ኃጢአት በመብዛቱ ማስጠንቀቂያ፤

ለ. በሳምራውያን እግዚአብሔር ቁጣ፤

ሐ. ለእሥራኤል ተስፋ ይገኝበታል::

## 7. ትንቢተ ሚክያስ

ሚክያስ እግዚአብሔርን የሚመስል ማን ነው? ማለት ሲሆን መጽሐፉ 7 ምዕራፎች አሉት። ስለማርያምና ኢየሩሳሌም መማረክና መመለስ፣ ስለጌታችን በቤተልሔም መወለድ /5፥4/ የተነበየ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ700 ዓመት በፊት የነበረ ነቢይ ነው።

## 8. ትንቢተ ኢዩኤል

ኢዩኤል እግዚአብሔር አምላክ ነው ማለት ሲሆን ከጌታ ልደት በፊት በ600 ዓመት የነበረ የይሁዳ ነቢይ ነው። መጽሐፉ 3 ምዕራፎች ያሉት ስለ ባቢሎን ምርኮ መልስ፣ ስለርዳታ መንፈስ ቅዱስ /የመንፈስ ቅዱስ መውረድ በሐዋርያት 2፥88/ ተንብዮአል።

## 9. ትንቢተ አብድዩ

አብድዩ የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ሲሆን፣ 600 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረ ነቢይ ነው። መጽሐፉ አንድ ምዕራፍ ያለው ስለ ኤዶምያስ /ኤሳው ወገኖች/ የተነበየ ነው።

## 10. ትንቢተ ዮናስ

ዮናስ ርግብ፣ የዋህ ማለት ነው። 900 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረ ሲሆን መጽሐፉ በአራት ምዕራፎች የተከፈለ፦

ሀ. ዮናስ እግዚአብሔር ከላከው ሀገር መኮብለሉ /በምዕ. 1-2/፤

ለ. በድጋሚ የዮናስ መላክና የነነዌ ንስሐ /ምዕ. 1-3/፤

ሐ. በነነዌ ሲደርስ የነበረው ጥፋት መመለሱ የነቢዩ ዮናስ አለመደሰት /ምዕ. 4/ የሚገልጽ ነው።

## 11. ትንቢተ ናሆም

ናሆም መጽናናት ማለት ሲሆን፣ 700 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረ ስለይሁዳ ሕዝብ ከአሦራውያን ነፃ መውጣት፣ ስለ ነነዌ ዳግም ጥፋት የተነበየ፤ መጽሐፉ በ3 ምዕራፎች የተከፈለ ነው።

## 12. ትንቢተ ዕንባቆም

ዕንባቆም ማቀፍ ማለት ሲሆን መጽሐፉ ሦስት ምዕራፎች ያሉት፣ የአይሁድ ሕዝብ በኃጢአቱ ስለሚደርስበት መከራ፣ ከለዳውያን በሚገዟቸው ላይ ባደረሱት ግፍ የሚደርስባቸው ቅጣትና ነቢዩ የጸለየውን ጸሎት የሚገልጽ ነው።

## 13. ትንቢተ ሶፎንያስ

700 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረ የይሁዳ ነቢይ ነው። መጽሐፉ 3 ምዕራፎች ሲኖሩት፦ አይሁድ እንዲመለሱ ምክርና ማስጠንቀቂያ፣ /1፥4-6፣ 12/ በኢየሩሳሌም አካባቢ ለሚገኙ ሕዝቦች ማስጠንቀቂያ /2፥4/ እና ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ 3፥8-13 እግዚአብሔር እሥራኤልና ይሁዳን በምርኮ እንደሚመልሳቸው 3፥14-20 ይገልጻል።

## 14. ትንቢተ ሐጌ

500 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የነበረ የይሁዳ ነቢይ ሲሆን በ3 ምዕራፍ የተከፈለ መጽሐፍ ነው። ስለ ቤተመቅደስ ዳግም መታነጽ ምዕ. 1፥4-15፣ ምዕ 2፥3-9 እግዚአብሔር ቀጣውን በበረከት እንደሚመልሰው ምዕ. 3፥11-19 ስለ ዘሩባቤል ምዕ. 3፥20-23 ይገልጻል።

## 15. ትንቢተ ዘካርያስ

ዘካርያስ እግዚአብሔር ያስተምራል ማለት ሲሆን 500 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረ ነው፡፡ መጽሐፉ 14 ምዕራፎች ሲኖሩት የአይሁድ ከምርኮ መመለስ የቤተመቅደስ መታደስ ስለኢያሱና ዘሩባቤል በኢየሩሳሌም ዙሪያ ላሉት አሕዛብም የተነገረ ትንቢት ሲኖረው ስለጌታችን ጎኑን በጦር መወጋት /12÷10/ የሐዋርያት ጌታ ሲያዝ መበተን /13÷7/ ስለሆሳዕና ምዕ.9 ስለዳግም ምጽአት /14÷5/ በተጨማሪም ስለአመቤታችን በወርቅ መቅረዝ ምዕ. 4÷3 ስለመላእክት ተራዳኢነት /1÷12-1/ ይገልጻል፡፡

## 16. ትንቢተ ሚልክያስ

ሚልክያስ ማለት መልእክተኛ ማለት ሲሆን 400 ዓመት ከጌታ ልደት በፊት የነበረ ነቢይ ነው፡፡ መጽሐፉ 4 ምዕራፎች ሲኖሩት፡-

ሀ. ስለአይሁድ ክህናትና ሕዝብ የተሰጠ የእግዚአብሔርን ተግሳጽ /1÷2/ ፤

ለ. ስለ አሥራት በኩራት የተነገረ ምርኩን ስለጌታችን መጥምቁ ዮሐንስ /2÷4/ ይገልጻል፡፡

# ሦሥሪፉ ስሦሜነት

## ሐዲስ ኪዳን

በዚህ ጥናታችን ያወንጌል፣ የታሪክ፣ የትምህርት /መልእክት/፣ የትንቢትና የሥርዓት ብሎን 35ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በአምስት እንከፍላቸዋለን:: ከእነዚህም በዚህ ምዕራፉትን የወንጌልን የታሪክ መጻሕፍትን በአንድ ላይ እንመለከታለን::

## ወንጌል

ዩአንጌልዩን /ኢቫንጌልዮን/ ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም ስብከት የምሥራች ማለት ነው:: ይህ የምሥራች እንደሚሰበክ አስቀድሞ በትንቢት፣ ኋላም በመላእክት የተሰበከ ሲሆን በመጀመሪያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኋላም ሐዋርያት ገልጸዋል:: /ኢሳ. 61÷1-2፣ ሉቃስ 4÷17፣ 2÷10፣ 24÷14፣ ማር.16÷15፣ ማቴ.4÷23፣ ሮሜ 1÷4/

ወልድ በሥጋ ተገልጾ ያደረገውን የማዳን ሥራ ለሰዎች የሰጠውን ከኃጢአትና ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ መውጣት ስለሚገልጽ ወንጌል የምሥራች ተብሏል:: ጸሐፊያኑም ወንጌላውያን ሲባሉ ማቴዎስና ዮሐንስ ከሐዋርያት ማርቆስና ሉቃስ ከአርድእት ናቸው::

ወንጌላውያን አራት ናቸው:: ምክንያቱም፦

- ❖ የጌታን ዙፋን ከሚሸከሙት 4ቱ እንስሳት ምሳሌ ወንጌላውያንም አራት ሆነዋል/ራዕይ 4÷7፣ ኢሳ.6÷2/
- ❖ ከአንድ ዕፀ ሕይወት ሥር መንጭተው ምድርን ከድርቀት ወደ ልምላሜ፣ ከልምላሜ ወደ አበባ፣ ከአበባ ወደ ፍሬ የሚያደርሱ አራት አፈላጋት /ወንዞች/ አሉ:: /ዘፍ. 2÷10-15/ ወንጌላውያንም አራት ሲሆኑ ከአንድ ጌታ ተምረው ዓለምን ከኃጢአት ወደ ንስሐ ከንስሐ ወደ ትሩፋት ከትሩፋት ወደ ክብር የሚያደርስ ወንጌልን ጽፈውልናል:: በእነዚህና በሌሎች ምክንያት ወንጌላውያን አራት ሆነዋል::

### 1. የማቴዎስ ወንጌል

1. ማቴዎስ የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ሲሆን አባቱ ዲቁ እናቱ ክሩትስያ ሲባሉ የዲቁ ሌላ ስም ደግሞ እልፍዮስ ነው:: /ማር. 2÷14/
2. የማቴዎስ የመጀመሪያ ስም ሌዊ ነበር:: ማቴዎስ ያሰው ጌታችን ነው::
3. ማቴዎስ ከቀራጭነት የተጠራ ሐዋርያ ሲሆን /ማቴ.9÷9/ ከዕርገት በኋላ ስርቅሊጦስ በፍልስጤም፣ በሕንድ፣ በኢትዮጵያ ያስተማረ ሐዋርያ ነው:: በመጨረሻም ጥቅምት 12 በሰማዕትነት አርፏል::
4. ማቴዎስ የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እያለ ምድራዊ ልደቱን ይጽፋልና በገጸ ሰብእ /ሰው/ ይመሰላል::
5. ማቴዎስ ወንጌሉን በዕብራይስጥ /በአረማይክ/ ቋንቋ ለዕብራውያን ጽፎላቸዋል፤ ይህም የነቢያትን ትንቢት ለሚያውቁ ነውና የጻፈው ከአብርሃም ጀምሮ እስከ ጌታችን በቆጠረው የትውልድ ቁጥርና ከሌሎች ወንጌላውያን በላይ አብዝቶ የብሉይን ኪዳን ጥቅሶችን በማቅረቡ ይታወቃል::

በተጨማሪ ታላቁ የቤተክርስቲያን አባት ጎርጎርዮስ ዘኢንዝናዙ "ማቴዎስ ለዕብራውያን ተአምራት ኢየሱስን ጻፈ" ሲል አረጋግጦልናል::

➢ ሰ28 ምዕራፎች የያዘው ወንጌል፦ ከምዕራፍ 1-2 ከልደት - ስደት እስከተመለሰበት፤

➢ ከምዕራፍ 3፥4-11 ጥምቀትና ጾም ከምዕራፍ 26-28 ከጸሎተ ሐሙስ ማታ እስከ እሑድ ትንሣኤ ያለውን ይገልጻል።

## 2. የማርቆስ ወንጌል

ቅዱስ ማርቆስ አባቱ አርስጦጥሎስ፣ እናቱ ማርያም ትባላለች። ማርቆስ የቀድሞ ስሙ ዮሐንስ እንደነበር ማርቆስ የተባለ ዮሐንስ ሲል የሐዋርያት ሥራ 12፥12፣ 12፥25፣ 15፥37 ይገልጽልናል።

- ማርቆስ የቅዱስ ጴጥሮስ ረድዕ ሲሆን፣ ከጌታችን በልጅነት እድሜው ተምሯል። በተጨማሪም ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ሐዋርያዊ ተልዕኮን ፈጽሟል።
- ማርቆስ በሮም ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር የተማረ ሲሆን ወደ ሰሜን አፍሪካ እስክንድርያና ወደተወለደበት ሀገር ሲረናይካ እና አካባቢው አስተምሮአል።
- በዚሁ አገልግሎት ላይ እንዳለም ሚያዝያ 30 በሰማዕትነት አርፎአል።
- ቅዱስ ማርቆስ ወንጌሉን ለሮማዉያን በሮማይስጥ ቋንቋ ራሱ የሚያውቀውን ከቅዱስ ጴጥሮስም እየተረዳ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ጽፎታል።
- ያለ እኛ ማን አለ? ብለው በሥጋዊ ኃይላቸው ስለሚመኩ ከእነርሱ በላይ ኃያል መኖሩን ለመግለጥ የጌታችንን ኃይል በደዌያት /በሽታ/፣ በአጋንንት፣ እና የማስተማር ሥልጣኑ ደግሞ ገልጧል። /1፥27፣ 1፥34፣ 1፥22/ ዋና ዓላማው /መልእክቱ/ የኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅነት መግለጥ ስለሆነ ሲጀምር /1፥1/ ሲያጠናቅቅ /15፥39/ በወንጌሉ ውስጥ /1፥11፣ 9፥7፣ 14፥61፣ 3፥11፣ 5፥7/ አስረግጦልናል፣ ይህን ያመኑትን ሮማውያንን ጠቅሷል።

ማርቆስ ዘአንበሳ ወይም በገጸ አንበሳ ይመሰላል። ምክንያቱም፦

1. አንበሳ ኑሮው በበረሃ ነው። በዚያ ሆኖ ሲጮህ ድምጹ በሩቅ ይሰማል። ማርቆስም ወንጌሉን ሲጽፍ በበረሃ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለ የመጥምቁ ዮሐንስን ትምህርትና ሥራ በማስቀደም ስለሚጀምር፣ /ማር. 1፥1-8/
2. በአንበሳ ድምፅ አራዊት ሲሸበሩ የቤት እንስሳት እንደሚገሠጹ /ወደ ማደሪያቸው እንደሚሰበሰቡ/ በማርቆስ ስብከት ኢ-አማንያን ተሸብረዋል፣ አማንያን ወደ ሃይማኖት ተመልሰዋል።
3. አንበሳ ለሳህም ጌታው ነው ይሰብረዋል። ቅዱስ ማርቆስ አምልኮተ ላሕምን በሙሴና በኤርምያስ ትምህርትና ተዓምራት እንኳ ባልተወቹ ግብጽ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ብሎ በመስበክ አምልኮተ ጣኦትን ከግብጽ አጥፍቷልና ዘአንበሳ ተብሏል። /ማር. 1፥1/

አከፋፈሉ፦ 16ቱን የማርቆስ ወንጌል ምዕራፋት በ6 ዐበይት ክፍሎች እንከፍላቸዋለን።

1. ለወንጌሉ የሰጠው ርዕስ /1፥1/
2. ጌታችን ከመዋዕለ ስብከቱ በፊት ያደረጋቸው /1፥2-13/
3. ጌታችን በገሊላና አካባቢው ያስተማረው ትምህርትና ገቢረ ተአምራቱ /1፥14፣ 9፥50/
4. ወደ ይሁዳ ገብቶ ያስተማረው ትምህርትና የሠራው ሥራ /10፥1፣ 14፥42/
5. ከሐሙስ ማታ እስከ ዓርብ ሰርክ ድረስ የነበረው የስቅለት ታሪክ /14፥43፣ 15፥47/
6. ትንሣኤ ዕርገት /16፥1-20/

## 3. የሉቃስ ወንጌል

ሉቃስ ከአሕዛብ ወገን የሆነ ወንጌላዊ ሲሆን፣ የሕክምና ባለሙያና በዓለም የነበረ ነው። /ቆላ. 4÷14/ ከ72 አርድእት አንዱ የሆነው ሉቃስ ከሐዋርያው የሐንስ ጋር ወደ ግሪክ ሄዶ በመቄዶንያ አስተምሯል። ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ሐዋርያዊ ጉዞዎችን በሚያደርግበት ጊዜ ያስተማረና መልእክት በማድረስ ይረዳው ነበር።

ቅዱስ ጳውሎስ በሰማዕትነት ካረፈ በኋላም በተሰያዩ ቦታዎች እየሰበከ ከቆየ በኋላ በ48 ዓመቱ በሰማዕትነት ጥቅምት 22 ቀን ዐረፈ።

- ቅዱስ ሉቃስ በድንግልናዊ ሕይወት የኖረ አባት ነው።
- ሉቃስ የክርስቶስ ምሳሌ የሆነውን "የሰባን ፍሪዳ /ላም/ አምጥታችሁ እረዱት" /ሉቃስ 15÷23/ ብሎ ስለጻፈና የጌታን በክብቶች በረት መወለድ ስለገለጸ "ዘላሕም" ይባላል። ወይም ከአራቱ እንስሳት በገጸ ላሕም ይመሰላል።
- ሉቃስ በ60 ዓ.ም. ገደማ በግሪኩ "የናኒ" ቋንቋ ቴዎፍሎዎስ ለተባለው ባለሥልጣን ወንጌሉን ጽፎለታል። /ሉቃስ 1÷1-4/
- የወንጌሉ ዓላማ በምዕራፍ 1÷1 "ስለተማርኸው ነገር እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ።" እንዳለው ቴዎፍሎስ በቃል የተማረውን በጽሑፍ ማስረጋገጥ ነው።

በዚህ ወንጌል 20 የጌታችን ታሪኮች በሌሎች ወንጌላት ያልተጠቀሱ ሲገኙ፣ ብዙ ተአምራት ተጽፈዋል። ከእነዚህም የ19ኙ ሙሉ ታሪካቸው ሲጻፍ አራቱ በወንጌል ሉቃስ ብቻ የሚገኙ ናቸው።

እነርሱም /7÷11-17፣ 13÷10-17፣ 14÷1-6፣ 17÷11-19/ የተጠቀሱት ናቸው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እምስት በቀጥር በቀጥታ ያስተማራቸው ሰባት በጥያቄ መነሻነት ያስተማራቸው በዚህ ወንጌል ብቻ የሚገኙ 12 ትምህርቶችን አካቷል።/5÷16-30፣ 14÷1-24፣ 14÷25-35፣ 16÷1-31፣ 18÷1-14፣ 10÷25-37፣ 11÷1-13፣ 12÷13-59፣ 13÷1-9፣ 15÷1-32፣ 17÷5-11፣ 17÷20-21/

- ሄያ እራት ምዕራፎች ያሉትን የሉቃስ ወንጌል ከፋፍለን ስናጠናው፦ ከምዕ. 1÷1-4 ወንጌሉን ለማን ለምንና እንዴት እንደጻፈው፤
- ከምዕ. 1÷4፣ 2÷52 የጌታችን ከጽንሰት ጀምሮ የሕፃንነት ዕድሜ ታሪኩ፤
- ከምዕ. 3÷1፣ 4÷13 ጥምቀትና ጾም፤
- ከምዕ. 4÷14፣ 9÷50 ጌታችን በገሊላና በዙሪያዋ ባሉ ከተሞች ያስተማረው ትምህርትና ተአምራቱ፤
- ከምዕ. 9÷51፣ 10÷37 ከገሊላ ወደ እየሩሳሌም በመንገዝ ላይ ሳለ ጌታችን የሠራውና ያስተማረው፤
- ከምዕ. 19÷28፣ 22÷46 ጌታ በኢየሩሳሌም በመጨረሻው ሳምንት ያደረገው፤
- ከምዕ. 22÷47፣ 23÷56 ጌታ ከተያዘበት ሐሙስ ማታ ጀምሮ በዓርብ ሰርክ በአዲስ መቃብር እስከተቀበረበት፤
- ከምዕ. 24÷1-53 ትንሣኤና ዕርገት።

በተጨማሪም የሉቃስ ወንጌል ስለሕፃብ ስለጸፊው "ወንጌለ አሕዛብ" "ሰባኪ መንፈስ ቅዱስ" ስለመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ደጋግሞ ስለገለጠ /1÷35፣ 12÷12፣ 4÷1፣ 11÷13/ ስለ እመቤታችንና ስለሌሎቹ ቅዱሳት አንስት /1÷5-56፣ 7÷7-17/ ስለጻፈው "ወንጌለ አንስት" በመባል ይጠራል።

## 4. የዮሐንስ ወንጌል

የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር የነጎድጓድ ልጆች በአረማይክ "ቦአኔርጌስ" ማር.3÷17 ሲባሉ፤ ጌታ ይወደው የነበረ /13÷23/፣ ነባቤ መለኮት /ታኦሎጎስ/፣ አቡቀለምሲስ /ባለራእይ/፣ ቁጹረ ገጽ /ፊቱ በሐዘን የተቋጠረ/ በመባል ይጠራል። ዮሐንስ ከዓሣ አጥማጅነት የተጠራ ሲሆን /ማቴ. 4÷21/ እስከ መስቀል አምላኩን ተከትሎ እመቤታችንን በአደራ የተረከበ /ዮሐ. 19÷26-27/ ከበዓለ ጰራቅሊጦስ በኋላ በቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በኢየሩሳሌምና አካባቢዋ እና በአንጾኪያ፤ ከዚህም ሌላ በሎዶቂያ በእስያ ከተሞች በተለይም በኤፌሶን አስተምሯል። በኤፌሶን በሚያስተምርበት ጊዜ ንጉሥ ድምጥያኖስ ስራሱ ምስል እንዲሰግድ ባዘዘበት ወቅት ዮሐንስ ይህን ተቃውሞ በፍጥሞ ተሰዷል። ሐዋርያው ዮሐንስ ከሌሎች ሐዋርያት ይልቅ ረዥም እድሜ በሕይወተ ሥጋ እስከ 96 ዓ.ም. ለ99 ዓመታት የቆየ፤ አስቀድሞ ጌታችን ቃል ኪዳን በገባለት መሠረትም /21÷22/ የተሠወረ አባት ነው።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በገጸ ንሥር ይመሰላል። ምክንያቱም፦

1. ንሥር በአግሩ ይሽከረከራል፤ በክንፉ መጥቆ ይበራል። ዮሐንስ ጌታችን በምድር የሠራውን ይጽፋል፤ ከሕልውናው ተገልጾለትም በመጀመሪያ ቃል ነበር /ዮሐ. 1÷1/ ብሎ ይጽፋልና።
2. የንሥር አይኑ ፅሩይ /የጠራ/ ነው። ሽቅብ ወጥቶ በሮ ቅንጣት ታህል ሥጋ ብትሆንም አትሠወረውም አንስቶ ይመገባል። እርሱም ምሥጢር ተገልጦለት ንጽሐ ሥጋን ንጽሐ ነፍስንና ንጽሐ ልቡና ተሰጥቶት ምሥጢረ መለኮትን ተናግሮአልና ነው።

ከአራቱ ወንጌላውያት መጨረሻ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በግሪክ ወንጌሉን የጻፈው ዮሐንስ ምሥጢረ መለኮትን አልቆ ሲያስረዳ በተመሰጠ እያለ መልአክ እግዚአብሔር ከባሕሩ በአንቀላል ቅርፊት ውኃውን እየቀዳ ወደ ደረቁ ምድር ሲገለብጥ ተመልክቶ እንዴት ይህን ባሕር በአንቀላል ቅርፊት ቀድተህ ስመጨረስ ትነግለህ? ብሎ ሲጠይቀው፤ መልአኩ እኔስ ፍጡርን ነው አንተ ተመራምሮ የማይደረስበትን ባሕርየ መለኮትን እመረምራለሁ ብለህ ትለፋ የለምን አለው። ያን ጊዜ ዮሐንስ የሥላሴን ምሥጢር ጠልቆ መመርመሩን አቁሞ ከእግዚአብሔር የተላከ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ ... ብሎ ሌላ ታሪክ ጀመረ። /ዮሐ. 1÷1-6/ በመጨረሻም ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀመዛሙርቱ ፊት አደረገ። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል። ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸው ይመስለኛል። ዮሐ. 20÷30-31፣ 21÷25 ሲል አጠናቋል። ከዚህ እንደምንረዳው፣

### የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈባቸው ዓላማዎች፦

1. ቅድመ ዓለም የነበረው እና ሥጋን የተዋሐደው /ትንቢት የተነገረለትን ሰባዔ የተቆጠረለት መሲህ የእግዚአብሔር ልጅ እርሱ መሆኑን/ በመግለጥና ማሳመን ነው። እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ ... ይህ ተጽፏል።


ሮ/ጨ/ግ/ሸ/ቅ/ገ/ጢ/ክ/ፊ/ኝ/ቤት

2. የዘለዓለም ሕይወት የሚገኝበትን መንገድ ለማስተማር ነው። ይህንን በተለያየ ትምህርት አጽንቷል። /3÷15፣ 5÷24-34፣ 6÷40፣ 51፣ 54፣ 10÷28፣ 11÷27፣ 12÷25፣ 17÷3 ... አምናችሁ በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፏል እንዲል።

እግዚአብሔር አምላክ በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ ስለ ዐረፈ ሰባት በሰብራውያን ፍጹም ቁጥር ነው። በዮሐንስ ወንጌልም በሰባት የተቀመሩ ነገሮች አሉ።

- <u>ሰባቱ "እኔ ነኝ"</u>

1. የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ /ዮሐ.6÷35/
2. የዓለም ብርሃን » /8÷12/
3. የበጎች በር » /10÷7/
4. መልካም እረኛ » /10÷1/
5. ትንሣኤና ሕይወት » /11÷25/
6. መንገድም፣ እውነትና ሕይወት እኔ ነኝ /14÷6/
7. እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ /15÷1/

- የእግዚአብሔር ልጅነቱን የሚመሰክሩ ሰባት ሰዎች፡- 1. መጥምቁ ዮሐንስ /ዮሐ.1÷29-36/ 2. እንድርያስ /ዮሐ.1÷41-42/ 3. ፊልጶስ /ዮሐ. 1÷46/ 4. ናትናኤል /ዮሐ. 1÷50/ 5. ማርታ /ዮሐ. 11÷27/ 6. ጴጥሮስ /ዮሐ. 6÷68-69/ 7. ቶማስ /ዮሐ. 20÷28/
- ከመሞቱ በፊት ያደረገው ሰባቱ ተአምራት፡- 1. የቃናው ሠርግ ተአምር /ዮሐ. 2÷1-11/ 2. የመኮንኑን ልጅ ማዳኑ /ዮሐ. 4÷46-54/ 3. መጻጉዕን ማዳኑን /ዮሐ. 5÷1-47/ 4. አምስት ሺህ ሕዝብ መመገቡ /ዮሐ. 6÷1-14/ 5. በባህር ላይ መሄዱ /ዮሐ. 6÷15-25/ 6. ዕውር ሆኖ የተወለደውን ማዳኑን /ዮሐ. 9÷1-41/ 7. አልዓዛርን ከሞት ማስነሳቱ /ዮሐ. 11÷1-14/
- የዮሐንስ ወንጌል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ፣ ትምህርትና ተአምራት የያዘው ቃል ከሌሎች ወንጌላት የተለየ ነው። ምክንያቱም ከላይ እንደተገለጸው የጻፈው ከሌሎች ወንጌላት በመጨረሻ ነውና ወንድሞቹ ያልገለጹትን የሌሎችን ዣየ በኋላ ገልጾአል/ጽፏል።

<u>አከፋፈሉ</u>፡-

በዮሐንስ ወንጌል የተጠቀሱ አራት የፋሲካ በዓላት አሉ /ዮሐ. 2÷13፣ 5÷1፣ 6÷4፣ 12÷1/ ፋሲካ በዓመት አንዴ ሚያዚያ 14 ቀን የሚከበር እሥራኤል ከሞት በኩር መዳናቸውን የሚያስቡበት በዓል ነው። ጌታችን በመዋዕለ ስብከቱ ሦስቱን ሲያከብር በአራተኛው ፋሲካ ግን ተሰቅሎአል። በዚህ መሠረትነት 21 የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፎችን በ7 እንከፍላለን። እነርሱም፡-

1. የጌታ ቅድመ ዓለም ሕልውናና በሥጋ መገለጡ ይህ መግቢያ ነው። /ዮሐ. 1÷1-8/
2. ከመጀመሪያው ዓመት ጥቂት ቀደም ብሎ በሦስቱ ወራት ውስጥ የተደረጉ ነገሮች/ዮሐ.1÷19፣ 2÷12/
3. በመጀመሪያው የማስተማር ዓመቱ ያደረጋቸው /ከም.ዕ. 2÷13፣ 4÷54/
4. በሁለተኛው የማስተማር ዓመቱ ያደረጋቸው /ከም.ዕ. 5÷1፣ 6÷71/
5. በሦስተኛው የማስተማር ዓመቱ ያደረጋቸው /ከም.ዕ. 7÷1፣ 12÷11/
6. በመጨረሻው ሳምንቱ የተደረጉ /ከም.ዕ. 12÷12፣ 21÷14/
7. የመደምደሚያ ትምህርቶች /21÷15-25/ ናቸው።

## የሐዋርያት ሥራ /የታሪክ ክፍል/

ሐዋርያ ሖረ ከሚለው የግእዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙ ተጓዥ ማለት ነው። ሐዋርያት በአይሁዳውያን ዘንድ አላዋቂ ከሚባሉት የተመረጡ ናቸው። 1ኛቆር. 1÷2-29፤ ያዕ. 2÷5-5፤ ሐዋርያት ብሎ ከሰየማቸው በኋላ ለጊዜው በምድረ እሥራኤል እየዞሩ መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያሉ እንዲያስተምሩ አዘዛቸው። ይህንንም ሥራ ለመፈጸም ሲሄዱ ለእግራቸው ጫማ ለእጃቸው በትር ለስንቃቸው ገንዘብ እንዳይዙ ክርስቶስ አስጠንቅቋቸው ነበር።

በተልእኳቸውም ድውይ ሲፈውሱ ሙት ሲያስነሱ ጋኔን ሲያስወጡና የወንጌልን ብርሀንነት ሲመሰክሩ በሕዝቡ ዘንድ ሞገስ አግኝተው ነበር። የዕለት ምግባቸውን አልተቸገሩም። ማቴ 10÷8-11። ሲያስተምሩ መከራና ሞትን እንዳይፈሩ በተከሰሱ ጊዜ ጠበቃ እንዳይፈልጉ በሚናገሩበት ጊዜ ምን እንናገራለን? ብለው እንዳይጨነቁ ነገራቸው። ይህንን የሚያበረታታ ቃል ስለተነገራቸው ተደፋፍረው ትልቅ መከራ ላይ እንዳይወድቁ በክፉዎች ዘንድ እንደ እባብ ጠቢባን በበጎዎች ዘንድ እንደ ርግብ የዋሀን እንዲሆኑ የምክር ቃል ጨመረላቸው። ማቴ. 10÷20-26። የሐዋርያት ሥራ የሚለውን መጽሐፍ የጻፈው ሉቃስ ነው። በዚህ መጽሐፈ በተለይ የቅዱስ ጳውሎስና የቅዱስ ጴጥሮስ የወንጌል ማስፋፋት ሥራ በሰፊው ተገልጿል። በተለይም ማቴ. 28÷19-20 እንደተገለጸው ወንጌልን ለዓለም እንዲያደርሱና እርሱም ሁልጊዜ ከእነርሱ ጋር መሆኑን ከነገራቸው በኋላ ወንጌልን እየሰበኩ ከክርስቶስ ፍቅር ምንም እንደማይለያቸው አውቀው ለዓለም እንዳዳረሱ እናያለን።

**አከፋፈሉ**፡-

1. ከምዕ. 1-8 ስለ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ይናገራል።
2. ከምዕ. 9-28 ስለ ቅዱስ ጳውሎስ ይናገራል።

## የትምህርት ክፍል

ትምህርት ክፍል የሚባሉት አጠቃላይ መልዕክታት መጻሕፍት ሲሆኑ የጸሐፊዎቹ ብዛት 5 ናቸው። እያንዳንዳቸው የጻፉትን ስንመለከት ደግሞ ጳውሎስ 14፤ ጴጥሮስ 2፤ ዮሐንስ 3፤ ያዕቆብ 1፤ ይሁዳ 1፤ በአጠቃላይ 21 ናቸው። መልዕክታት በ3 ይከፈላሉ።

1. ስግንበር የተሳክ መልእክት ሮሜ፤ ፊልጵስዩስ . . . ወዘተ . . .
2. ስግል የተሳክ መልእክት ፊልሞና፤ ጢሞቴዎስ፤ ቲቶ፤ 2ኛ ዮሐ. መልዕክት
3. ስዓለም አቀፍ መልእክት የዕብራውያን መልእክት ስእሥራኤል ዘስጋ እሥራኤል ዘነፍስ እንዲሁም 1ኛ ዮሐንስ መልእክት።

ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ስሙን አልጻፈም። ይህም የሆነበት ምክንያት፣

- ቅዱስ ጳውሎስ ክርስትናን የተቀበለው ከእነርሱ መሀል ስለሆነና አይሁዳውያን ደግሞ የእነርሱን ሕግ የሚሽርባቸው ከተገኘ ስለማይቀበሉት እርሱ መጻፉን ካወቁ ትዛኤውን በትነው የመልእክቱን ሃሳብ ሳይረዱ እንዳይቀሩ በማለት ስሙን ሳይጽፍ ቀረ።

## 1. ወደ ሮሜ ሰዎች የተጻፈ

ይህን መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ በሮም ከተማ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች የጻፈው ነው። ዘመኑም በ57 ዓ.ም. ገደማ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮም ሄዶ ስለነበረ የክርስቶስን ወንጌል ከቆሮንቶስ ሆኖ እስኪሄድ ድረስ ጻፈላቸው። ብዙውን ጊዜ በደብዳቤ ትምህርቱን ይልክ ነበርና።

<u>አከፋፈሉ</u>፡-

1/ ስለ አረማውያን፣ ስለአይሁድ፣ ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ አስፈላጊነት /ምዕ. 1-3/

2/ የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሰው በእምነት መቅጠሩ /ከምዕ. 4-5/

3/ ሰው ከጸደቀ ከኃጢአት ከሕግ ከሞት ኃይል ነፃ መሆኑ /ከምዕ. 6-8/

4/ የእስራኤል መመረጥና ተስፋቸው /ከምዕ. 9-11/

5/ የምእመናን አካሄድ በዓለም፣ በግልና በቤተክርስቲያን /ከምዕ. 12-14/

6/ ስብከት /ምዕ. 15/

7/ ሰላምታና አደራ /ምዕ. 16/

## 2. 1ኛው የቆሮንቶስ ሰዎች መልዕክት

ይህች ከተማ ደግሪክ ነች። በዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ማኅበር አቋቁሞበት ነበር። የሐዋ. ሥራ ምዕ. 18 በዚህ ማኅበር ውስጥ ክርክር መለያየትና ዝሙት ስለነበር ሐዋርያው ስለነዚህ ነገሮች ምክሩን ለመስጠት መልእክቱን ጻፈ።

1/ ስለ ቤተክርስቲያንና በመካከላቸው ስለተነሳው ችግር /ከምዕ. 1-4/

2/ በመካከላቸው ስለተፈጸመው ዝሙት /ከምዕ. 5-6/

3/ ስለ መጋባት /ምዕ. 7/

4/ ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ /ከምዕ. 8-10/

5/ ስለ ቅዱስ ቁርባን /ምዕ. 11/

6/ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች /ከምዕ. 12-14/

7/ ስለ ትንሣኤ ሙታንና ዳግም ምጽአት /ምዕ. 15/

8/ ገንዘብ ስለማዋጣትና ስለ ግሉ ጉዳይ /ምዕ. 16/

## 3. <u>ሁለተኛይቱ የቆሮንቶስ ሰዎች መልእክት</u>

በቆሮንቶስ ያሉት ክርስቲያኖች የመጀመሪያውን መልእክት ሳይቀበሉ ቀርተው ሳለ ጳውሎስም ሄዶ ቢመክራቸው ተቃውመውት ወደ ኤፌሶንም ተመልሶ ከባድ መልእክት ለቲቶ ሳከው /ምዕ. 2/ መልእክቱን ከሰሙ በኋላ ደነገጡና ታላቅ ሀዘን አዘኑ፤ ተፀፀቱ መከራን ለመቀበል ተዘጋጁ። ቲቶ ይህንንም ለቅዱስ ጳውሎስ ነገረው፤ ቅዱስ ጳውሎስ በመቄዶንያ ሳለ ይህችን ሁለተኛይቱን መልእክት ጻፈላቸው። ዘመኑም በ56 ዓ.ም. ነው።

<u>አከፋፈሉ</u>፡-

> በቆሮንቶስ ማኅበር ምክንያት ስለደረሰበት መከራ ከምዕ. 1-2

## 4. ወደ ገላትያ ሰዎች የተላከ መልእክት

ገላትያ የሚገኘው ዛሬ ቱርክ በሚባለው ሀገር ውስጥ ነው። የገላትያ ቤተክርስቲያኖች የተመሠረቱት በቅዱስ ጳውሎስ ነው። የሐዋርያትን ትምህርት እየነቀፉ ካልተገረዛችሁ የሙሴን ሕግ ካልጠበቃችሁ ማመን ብቻ አይበቃም በማለት የሚያስተምሩትን ሐዋርያው ሰምቶ ይህችን መልእክት ጻፈ። ይኸውም መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ ከጻፋቸው የመጀመሪያው ነው። ጊዜውም ከ48-49 ዓ.ም. ይሆናል።

**አከፋፈሉ፦**

1. የወንጌልን እውነተኛነት ያረጋግጣል። ከምዕ. 1 - ምዕ. 2
2. ክርስቲያን ከሕግ ባርነት ነፃ መሆኑን ያረጋግጣል። ከምዕ. 3 - ምዕ. 4
3. ክርስቲያን ተገቢ አኗኗር አለው። ምዕ. 5 - ምዕ. 4

## 5. ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተላከ

ቅዱስ ጳውሎስ በ43 ዓ.ም. በመጀመሪያው መንገድ ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር ከቆሮንቶስ ወጥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ጥቂት ወራት በኤፌሶን ቆይቶ ነበር። ነገር ግን በ49 ዓ.ም. በሁለተኛው መንገዱ ኤፌሶን ደርሶ ሁለት ዓመት ከሦስት ወር እያስተማረ ቆየ በኋላ የአርጤምስን ምስል ከሚሠራው ከአንጥረኛው ከድሜጥሮስ ጋር በተነሳው ጭቅጭቅ ከኤፌሶን ወጥቶ ወደ መቄዶንያ ሲሄድ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ጢሞቴዎስን ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሹሞላቸው ሄደ እንጂ ጠብቁ እንደሌላቸው በጎች በተኩላ መካከል ትቷቸው አልሄደም።

ከዚህ በኋላ በ56 ዓ.ም. ታስሮ ወደ ሮማ ከሄደ በኋላ የኤፌሶን ሰዎች በሃይማኖት መጽናታቸውን በሰማ ጊዜ በሃይማኖታቸው ስለጸኑ በሰማይ የሚያገኙትን ዋጋ ገልጦ ለማስረዳት ወደፊትም በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ ለማድረግ ስለሰበ ይህን መልእክት ሊጽፍላቸው ጀመረ።

- ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ለማያዊ ርስት መቀበላቸው። ኤፌ. 1-15
- በኃጢአት ብዛት ከክርስቶስ ተለይተው ሲኖሩ በሃይማኖት መቅረባቸውንና ወደ ተስፋው መግባታቸው።
- ከተስፋው ርቃችሁ ለነበራችሁት /ለአህዛብ/ ቀርበው ለነበሩት ለአይሁድ የምሥራች ቃል ኢሳ.57÷19፣ ዘካ.9÷10።

ከእንግዲህ ወዲህ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች የቅዱሳንም ባላገሮች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በነቢያትና በሐዋርያት መሠረትነት ላይ ተሠርታችኋልና። የማዕዘኑም ራስ ክርስቶስ ነው። በማዕዘኑም ደንጊያ ላይ ሥራው ሁሉ ጸንቶበት ይኖራል ይላቸዋል። ኤፌ. 2÷1-22።

## 6. ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች የተላከ

ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ወንድሞች ሆይ የክርስቶስ ሕግ ወንጌልን ለማስተማር ዝናዬና ስለ ክርስቶስም የታሠርሁት አሥራቴ ፈጽሞ በሰው ሁሉ ዘንድ እንደተሰማ እንድታውቁ እወዳለሁ። ቅዱስ ጳውሎስ ታሥሮ ሳለ ከሰዎች ወገን አስሌቶቹ መምህር እርሱ ብቻውን ይቆጨው ይንደደው እኛም እናስተምራለን እያሉ በምቀኝነት የክርስቶስን ነገር የሚያስተምሩ ነበሩ። አስሌቶቹ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ ስለታሠረ ትምህርቱ እንዳይቀር እያሉ በእውነትና በፍቅር የክርስቶስን ትምህርት የሚያስተምሩ ነበሩ። በዚህም ነገር ጳውሎስ አላዘነም። ለዚህም ሲጽፍላቸው በምቀኝነትም ሆነ በፍቅር ሁሉም እንጂ አላዝንም ብሎአቸዋል። ፊል. 2÷1-12። አይሁድ እርሱን የሚያሳዝን ሥራ ከመሥራት አያርፉምና ከውሾች ተጠበቁ

በማለት ጽፎላቸዋል:: እውነተኞች ግዝረትን እግዚአብሔርን በመንፈስ የምናመልከው እኛ ነን በሥጋ ግዝረት አንመካምና:: መመካትም ቢያስፈልግ ፈሪሳዊ ክብር እኔ እበልጣቸዋለሁ ብሏቸዋል:: ፊልጵ.3÷27::

## 7. ወደ ቆላስዮስ ሰዎች የተላከ መልዕክት

ቆላስዮስ ዛሬ ቱርክ በሚባል ሀገር ትገኛለች:: ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን መልእክት የጻፈው በሁለት ምክንያት ነው:: 1ኛ. የቆላስዮስ ተወላጅ አናሲሞስ ወደ ሀገሩ ስለሚመለስ ለቤተ ክርስቲያን መጻፉ::

2ኛ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሐሰት ትምህርት ስለነበረ ሐዋርያው የማስጠንቀቂያ መልእክት ሊጽፍላቸው ችሏል:: በ62 ዓ.ም.ገደማ ተጽፏል::

አከፋፈሉ:-

1.የሐዋርያው ምስጋና ጸሎት እንዲሁም ክርስቶስ የሁሉ ጌታና ፍጹም መድኅን ስለመሆኑ፤ ምዕ. 1

2.ከሐሰት ትምህርት እንዲጠበቁ ፤ ምዕ. 2

3.ስለክርስቲያናዊ ኑሮ፤ ምዕ. 3

4. አብረውት ስለሚሠሩ ሰዎች ሰላምታ፤ ምዕ. 4÷7፣8÷18

## ፰. አንደኛው ወደ የተሰሎንቄ ሰዎች የተላከ መልእክት

በግሪክ አውራጃ ዋና ከተማ ነበረች:: ሐዋርያው መልዕክቱን የጻፈው በ51 ዓ.ም. ገደማ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ በዚህች አገር አስተምሯል:: ሆኖም መሠረታዊ ትምህርትን ሊያስተምራቸው ስለፈለገ ሁለቱንም ጻፈላቸው:: የመጀመሪያው መልእክት አከፋፈል:-

1.የሐዋርያው ምስጋና፤ ምዕ. 1

2.የሐዋርያው ገድል በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን፤ ምዕ. 2÷1-16

3.ስለ ተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን የሐዋርያው ስጋት፤ ምዕ. 2÷17፣ ምዕ. 3÷13

4.ስለ ምእመናን ቅድስናና ፍቅር፤ ምዕ. 1÷12

5.ስለ ጌታ ዳግም ምጽአት፤ ምዕ. 1÷12

6. ስለ ምእመናን በኅብረት መኖር፤ ምዕ. 5÷12-28

## 9. ሁለተኛው የተሰሎንቄ ሰዎች የተላከ መልእክት

አከፋፈሉ:-

1. ክርስቲያንና መከራው፤ ምዕ. 1

2.ክርስቲያንና ዳግም ምጽአት፤ ምዕ. 2

3. ክርስቲያንና ዕለታዊ ተግባሩ፤ ምዕ. 3

## 10. 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ የተላከ መልእክት

ጢሞቴዎስ ሐዋርያው ጳውሎስ በልስጥራን ያገኘው ወጣት ነው:: ይህም ልጅ የቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጅ ነበር:: በሄደበት ሁሉ ይሄድ ነበር:: 2ኛቆሮ.1÷1፣ ፊልጵ.1÷1-2፣ ተሰሎ.1÷1:: ሐዋርያው ለጢሞቴዎስ ሁለት መልእክት ጽፎለታል:: ጢሞቴዎስን ለማበረታታት ጽፎለታል:: 1ኛጢሞ. 1÷3-7 ዘመኑ በ63 ዓ.ም. ገደማ ነበር::

**አከፋፈሉ:-**

1. ስለ ጳውሎስና ስለ ጢሞቴዎስ፣ ምዕ. 1
2. ስለ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ሥርዓትና አስተዳደር፣ ምዕ. 26
3. ልዩ ልዩ ትዕዛዝና ምክር፣ ምዕ. 6

## 11. 2ኛ ለጢሞቴዎስ የተላከ መልእክት

ይህች መልእክት ሐዋርያው ጳውሎስ በመጨረሻ የጻፋት የመሰነባበቻ መልእክት ናት። የጻፋት ከመሞቱ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ በ64 ዓ.ም. ገደማ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል። 2ኛጢሞ. 4÷6-8 መልእክቱን የጻፈበት በተጨማሪ የተቀበለውን አደራ እንዲጠብቅና በትምህርቱ ጸንቶ እንዲኖር ያሳስባል። 2ኛ. ጢሞ. 1÷6-14፣ ምዕ. 21፣ 3÷14-17።

**አከፋፈሉ:-**

1. የተወደደ ልጁን ያደፋፍራል፣ ምዕ. 1
2. ስለ ቤተክርስቲያን ሥራ ይመክረዋል፣ ምዕ. 2
3. ስለሚመጣው አስጨናቂ ዘመን ያስጠነቅቀዋል፣ ምዕ.3
4. ወንጌልን ስመስበክ እያነሳሳው ስለመሞቱ ያስታውቀዋል፣ ምዕ.4

## 12. ወደ ቲቶ የተላከ መልእክት

ቲቶ እንደ ጢሞቲዎስ ለቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጅ ነበር። ቲቶ ለድሆች ቅዱሳን ገንዘብ ስመሰብሰብ ወደ ቆሮንቶስ ተልኳል። 2ኛ.ቆር.7÷5-7፣ 1ኛቆር.16÷1፣ 2ኛቆር. 8÷6-16። ቤተክርስቲያንን እንዲያደራጅ በቀርጤስ ትቶት ነበር። ቲቶ 1÷5-6። ይህ መልእክት ለቲቶ ሲጻፍ የመጀመሪያው ነው። ዘመኑ በ63 ዓ.ም. ነው።

**አከፋፈሉ:-**

1. በቀርጤስ ያሉትው የቤተክርስቲያን አስተዳደር፣ ምዕ.1
2. ቲቶ የቤተክርስቲያን መሪ ሆኖ መልካም አርዓያ እንዲሆን፣ ምዕ. 2
3. ቲቶ ተጠንቅቆ ግብረ ግብነትን እንዲያስተምር፣ ምዕ. 3

## 13. ወደ ፊልሞና የተላከች መልእክት

ፊልሞና በቆላስይስ የኖረና ወንጌልን ከሐዋርያው ጳውሎስ የሰማ ሰው ነው። ፊልሞ ምዕ. 2። አናሲሞስ የተባለ ባሪያ አገልጋይ ነበረው። ተጣልተውም ስለነበር አናሲሞስን ከፊልሞና ጋር ለማስታረቅ ጻፈው። ፊልሞና ክርስቲያን የሆነው በቅዱስ ጳውሎስ ምክንያት ነው። መልእክቱ በ62 ዓ.ም. ተጽፏል። አንድ ምዕራፍ ብቻ አለው።

## 14. ወደ ዕብራውያን ሰዎች የተላከ

በአንድ ቦታ ለሚገኙ ዕብራውያን ወይም አይሁድ የተላከ መልእክት ነው። በመልእክቱ የቅዱሱ ጳውሎስ ስም አልተጠቀሰበትም። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ:-

1. ቅዱስ ጳውሎስ ክርስትና የተቀበለው ከእነርሱ መሀል ስለነበርና አይሁዳውያን ደግሞ የእነርሱን ሕግ የሚሽርባቸው ከተገኘ ስለማይቀበሉት እርሱ መጻፉን ካወቁ ጉባዔውን በትነው የመልእክቱን ሐሳብ ሳይረዱ እንዳይቀሩ በማለት ስሙን አልጻፈም።

2. ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን መልእክት የጻፈው ሮም በቁም እሥር ላይ እያለ በመሆኑ በግዞትና በጦርነት ጊዜ መተማመን ስለማይኖር ሮማውያን ካወቁ ወገኖቹን ያጎሳቁሉናል ብለው እንዳይቃወሙት ነው::

ይህንን መልእክት አንዳንዶች አገላለጡ ለየት ያለ ነው ብሚለት በርናባስ፣ አጵሎስ፣ ቀለሚንጦስ ጽፈውታል ይላሉ:: ሌሎች ግን ቅዱስ ጳውሎስ የአይሁድ ሊቅ በመሆኑ ገላ. 1÷14 ለየት ባለ አገላለጽ ጽፎት ነው ይላሉ:: ዓላማው ዕብራውያን ወደ አይሁድ ብማፈግፈግ ክርስቶስን እንዳይክዱ ነው ይላሉ::

**__አከፋፈሉ፡-__**

1. ከሙሴና ከቃሉ ክርስቶስና ቃሉ ይበልጣል፤ ምዕ. 1-5
2. ከአሮንና ከክህነቱ ክርስቶስና ክህነቱ ይበልጣል፤ ምዕ. 5-7
3. ከብሉይ ኪዳን ክርስቶስ ያደረጀው ሐዲስ ኪዳን ይሻላል፤ ምዕ. 8-10
4. የአማኞች እርምጃና ኑሮ፤ ምዕ. 11-13

## 15. __1ኛ የጴጥሮስ መልእክት__

ይህንን መልእክት የጻፈው በመከራና በስደት ጊዜ ነው:: ጴጥሮስ ከ12 ሐዋርያት አንዱና አዕማድ ከተባሉት ዋነኛው ነው:: የመጀመሪያ ስሙ ስምዖን ሲሆን በኋላ በጌታችን ኬፋ ተብሎ ተሰይሟል:: ኬፋ የሚለው በአረማይክ ሲሆን በግሪክ ጴጥሮስ ማለት ነው:: ትርጉሙ ሁለት ማለት ነው:: ማር. 3÷16፣ ዮሐ. 1÷43:: ሥራው ዓሣ አጥማጅ፣ ሚስትም ነበረችው:: ማር. 1÷26-30፣ ማር. 1÷16:: ከዕርገት በኋላ የክርስቲያኖች መሪ ነበር:: የሐዋ. 1÷14-22:: በኔሮን ዘመነ መንግሥት በሮሜ ከተማ ቁልቁል ተሰቅሎ ሞቷል /በክብር/:: እንዲሁም ሥልጣን የተሰጠው የሐዋርያት መሪ ነው:: ማቴ. 16÷18-19 የተጻፈው በ63 ዓ.ም. ነው::

**__አከፋፈሉ፡-__**

1. ስለተዘጋጀ መዳን፤ ምዕ. 1÷1-12
2. ስለተጠራንበት ቅድስና፤ ምዕ. 1፥13፣ ምዕ. 2፥10
3. ስለታቀደልን መልካም ኑሮና ስለምንቀበለው መከራ፤ ምዕ. 2፥11፣ ምዕ. 4፥19
4. ስለሚገባው ማኅበራዊ ትጋት፤ ምዕ. 5፥1-11

## 16. __2ኛ የጴጥሮስ መልእክት__

በድጋሚ የጻፈበት ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ሾልከው ገብተው የሐሰት ትምህርት ያስተምሩ ነበርና አንባቢዎችን ሊያስጠነቅቅ ነው:: በ64 ዓ.ም. ገደማ ጽፎታል::

**__አከፋፈሉ፡-__**

1. ስለ ተስፋፋላቸው የወንጌል እውነተኛነት፤ ምዕ.1
2. ስለ ሐሰተኞች አስተማሪዎች መነሳት ትምህርት፤ ምዕ.2
3. የጌታ ቃልን መጠበቅና መጠንቀቅ፤ ምዕ.3

## 17. __1ኛ የዮሐንስ መልእክት__

ሐዋርያው ዮሐንስ በኤፌሶን ተቀምጦ ሳለ ይህንን መልእክት በ90 ዓ.ም. ገደማ ጽፏታል:: የጻፈው እስያ በሚገኙት አውራጃ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ከተሳሳተ ትምህርት ሊያስጠነቅቃቸው ነው:: ምዕ. 2÷18-27::

**አስፈላጊ**:-

1. ትእዛዙን መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን፤ ምዕ. 1÷5፣ ምዕ. 2÷6፣ ምዕ. 1÷10
2. እርስ በእርሳቸው መዋደድ እንደሚገባቸው፤ ምዕ. 2÷7-17፣ ምዕ. 3÷11-24
3. የሐዋርያትን ትምህርት አጽንቶ መያዝ፤ ምዕ. 2÷18-29፣ 4÷1-6፣ 5÷1-12

## 18. 2ኛ የዮሐንስ መልእክት

እንደ መጀመሪያው መልእክት ሆኖ ይህችም በሐዋርያው በዮሐንስ በኤፌሶን ከተማ በ90 ዓ.ም. ተጽፏል። በመልእክቱም ለአንዲት ሴት ጽፎ ከመናፍቃን ትምህርት እንድትጠበቅ ያስጠነቅቃታል።

## 19. 3ኛ የዮሐንስ መልክት

ይህች መልእክት የተጻፈችው እንደ ሁለቱ መልእክት ሲሆን የሐንስ ጋይዮስ ወደ ተባለ አማኝ ሰው ጽፎ እንግዶችን ስለሚቀበል ያመሰግነውና በዚያች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚገባው መስያየት በመናገር መልካም ያደረገውን እንዱን ሰው ይደግፋል።

## 20. የያዕቆብ መልዕክት

ያዕቆብ የዮሐንስ ታላቅ ወንድም የዘብዴዎስ ልጅ ነው። ከሐዋርያት አንዱ ሲሆን የጌታ ወንድም ይባላል። ማቴ. 10÷2፣ ማቴ. 13÷55። ከጴጥሮስ በኋላ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ዋና መሪ ሆኗል። የኢየሩሳሌም ሲኖዶስ ሊቀመንበር ነበር። የሐዋ. 12÷17፣ 15÷13-22። በ62 ዓ.ም. ክርስትናን ለተቀበሉ አይሁድ ነው። በመከራ ላይ ስለነበሩ ሊያጽናናቸውና ስህተታቸውን ሊያርም ጽፎላቸዋል። ዋና ስህተታቸው እምነታቸውን በሥራ አይገልጹምና ያዕቆብ ይህንን በሰፋት ገልጾታል። መልእክቱ በ50 ዓ.ም. ገደማ ተጽፏል።

1. በመከራ ላሉ ያጽናናቸዋል፤ ምዕ. 1
2. ልዩ ልዩ ስህተቶችን ያርማቸዋል፤ ምዕ. 24
3. ስትዕግስትና ስጸሎት ያነሳሳል፤ ምዕ. 5

## 4. የይሁዳ መልእክት

የኢየሱስ ወንድሞች ከተባሉት አንዱ ነው። ማቴ. 13÷55። ይህን መልዕክት ምእመናን ያገቡት ነበር። ሐሰተኞችን ለማስጠንቀቅ ትምህርታቸውን ለመቃወም ብሎ ጻፈላቸው ዘመኑም በ94 ዓ.ም. ነው። ይሁዳ የሄኖክን መጽሐፍ ጠቅሷል። ምዕ. 1÷14-15።

# ዮትንቢት ክፍል

## የዮሐንስ ራዕይ

በምዕ. 1 ቁ. 1 ላይ እንደምናነበው ሁሉ ይህ የትንቢት መጽሐፍ በመልአኩ በኩል ለዮሐንስ ያመለከተው ራዕይ ነው። ራዕዩን የጻፈው በእስያ አውራጃ ለነበሩት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ነው።

ዮሐንስ ራዕዩን የጻፈው በሽምግልናው ዘመን ነው። ይኸውም በፍጥም ደሴት ላይ ታስሮ ሳለ በ96 ዓ.ም. ገደማ ነው።

__አስፋፊሉ፡-__


1. ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ስለጻፈው መልእክቶች፤ ምዕ. 1-3
2. በሰማያት ስለሚሆኑ ነገሮች አንደኛው ገለጻ፤ ምዕ. 4-5
3. ስለ ሰባቱ ማኅተሞችና ስለ ሰባቱ መልእክቶች፤ ምዕ. 6-11
4. ስለ ዘንዶው፣ ስለ አውሬው ፣ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት፤ ምዕ. 12-13
5. በሰማያት ስለሚሆኑ ነገሮች 2ኛ ገለጻ፤ ምዕ. 14
6. ስለ ሰባቱ ጽዋዎች፤ ምዕ. 15-16
7. ስለ ባቢሎን መፍረስ፤ ምዕ. 17-19
8. ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መቋቋም፤ ምዕ. 20-22


ወስብሐት ለእግዚአብሔር

በመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት

ትምህርት ክፍል ተዘጋጀ።


☎ 55 89 41

✉ 27314


__፲፱፻፺፪__ ዓ.ም.